፳ ፤ መለኮት ፤ የእምላክነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፤ ሥጋም የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ እንልም ፤ እንደ ፡ መጥፎ ፡ አሳባቸውም ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፤ ይህን ፡ በመናገራቸው ፡ ሁለት ፡ አካል ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ያመጣሉ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የተጠሉ ፤ የተ ነቀፉ ፡ ናቸው ፤ ከእኛ ፤ ሃይማኖታቸው ፡ ከቀና፡በው ነት ፤ በቅንነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከጠበቁ ፤ ከአባቶቻችን ፡ ትምህርትም ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። ወደ ፡ እነዚያ ፡ ዐላውያን ፡ ክሕደትም ፡ እንግባ ።

ዘአትናቴዎስ ፡ ም ፡ ፻፯ ። ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፯ ።

ዘአትናቴዎስ ፡ ም ፡ ፻፯ ። ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፯ ።

፳፩ ፤ ወዳእሙ ፡ ንሕነሰ ፡ ንትአመን ፡ ከመ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አምላክነ ፡ ውእቱ ፡ ዐማኑኤል ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ እግዚእ ፡ ወ፩ዱ ፡ መሲሕ ፡ ወ፩ዱ ወልድ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካል ፡ ወ፩ዱ ፡ ገጽ ፡ ቃል ፡ ዘተ ዋሕደ ፡ ወተሠገወ ፡ እምኀቱ ፡ ህላዌያት ፡ ወእም ኀቱ ፡ አካላት ፡ ዘውእቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትስብ እት ፡ ወኮኑ ፡ ኀሦሙ ፡ ፩ደ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ደ ፡ ምግባረ ወንትአመን ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ወሰ ብእ ፡ ኅቡረ ፡ ወይትዔረዮ ፡ ለአብ ፡ በህላዌ ፡ መለ ኮቱ ፡ ወይትዔረየን ፡ ለን ፡ በህላዌ ፡ ትስብእቱ ።

፳፪ ፤ ወቦቱ ፡ አካል ፡ ሉዐላዊ ፡ አምላካዊ ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ እስመ ፡ ለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ወገብረ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ በኀይለ ፡ መለኮቱ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ እምትስብእቱ ፡ ወግብራ ተሂ ፡ ትሑታተ ፡ ረሰየ ፡ ሎቱ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ረኀብ ፡ ወጽምእ ፡ ወድካም ፡ ወዘይመስሎሙ ፡ ለእሉ ፡ ወሐመ ፡ በሕማመ ፡ ሥጋ ፡ ማሕየዊት ፡ በፈቃዱ ፡ ወሞተ ፡ በዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ በእን ቲአነ ።

፳፫ ፤ ወንአምን ፡ ዓዲ ፡ በትንሣኤሁ ፡ እምድኀረ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕል ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ቀተሎ ፡ ለሞት ፡ በሞቱ ፡ ወሰዐረ ፡ ሕማመ ፡ እምኔነ ፡ ወእንሥእነ ፡ ምስሌሁ ፡ ወረሰየነ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ኢሐማምያነ ፡ ወኢንስእል ፡ ወኢንርሐቅ ፡ እምነ ፡ ጽድቅ ፡ ወኢንት ወለጥ ፡ ወአሰፈወነ ፡ ሕይወተ ፡ ብፅዕተ ፡ እንተ ፡ ኢተኀልፍ ፡ ወኢተኀልቅ ።

፳፬ ፤ ወእለሰ ፡ ይብሉ ፡ ከመ ፡ ሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ ለእግ ዚእነ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ደነስ ፡ እምሰማይ ፡ አው ፡ እምካ ልኢ ፡ ፍና ፡ አው ፡ አልቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ወልቡና ፡ አው ፡ ኢየሐምም ፡ ወኢይመውት ፡ አለሰ ፡ ይብሉ ዘንተ ፡ ይከውኑ ፡ በኀቤነ ፡ ከመ ፡ አብዳን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ልብ ፡ ወአእምሮ ፡ ወንሕነሰ ፡ ናርሕቅ ፡ ኪያሆሙ ፡ ወናወግዘሙ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወለዙ ሎሙ ፡ ዓላውያን ፡ አዕራረ ፡ ጽድቅ ፡ ወተላውያነ ፡ ሐሰት ፡ በከንቱ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ እመልእከተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአቡነ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ወዘምሥራቅ ፡ ኅበ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአስክንድርያ ፡ ወግብጽ ፡ ወእለ ፡ ምስሌሃ ፡ ንዌጥን ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ንሬሲ ፡ ተስፋነ ፡ ላዕለ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ እለ ፡ ዕሩያን ፡ በመለኮት ፡ ወእ ሐቲ ፡ ኃይል ፡ ወአሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወ፩ዱ ፡ መን ግሥት ፡ ወአሐቲ ፡ ፈቃድ ፡ ወ፩ዱ ፡ ሥምረት ፡ ዘውእቶሙ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይቲ ፡ አካላት ፡ ወይቱ ፡ ገጻት ፡ እለ ፡ ዕሩያን ፡ በ፩ዱ መለኮት ፡ ይሰገዱ ፡ በአሐቲ ፡ ስግደት ።

፳፩ ፤ እኛስ ፡ ከሁለት ፡ ባሕርያት ፤ ከሁለት ፡ አካላት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ አንድ ፡ ወልድ ፡ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ ቢሆን ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔር አምላካችን ፡ ዐማኑኤል ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ እናምናለን እነዚህም ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ናቸው ፤ ሁለ ቱም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ ግብር ፡ ሆኑ ፤ አሁ ንም ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ እንደሆነ ፡ እናምና ለን ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አብን ፡ ይመስለዋል ፤ በባሕርየ ፡ ትስብእቱም ፡ እኛን ፡ ይመስለናል ።

፳፪ ፤ ለመለኮቱ ፡ እንደሚገባ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ አካል ፡ አለው ፤ እርሱ ፡ አምላክ ነውና ፡ ከሥጋው ፡ ሳይለይ ፡ በሥልጣኑ ፡ መለኮቱ ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ፤ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ሥራንም ሠራ ፤ የድካም ፡ ሥራዎችንም ፡ ለእሱ ፡ ገንዘብ አደረገ ፤ እነዚህም ፡ ረኀብ ፤ ጽምእ ፤ ድካም ፤ እነዚ ህንም ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ፤ በፈቃዱም ፡ የምታ ድን ፡ የሥጋ ፡ ሕማምን ፡ ታመመ ፤ ስለ ፡ እኛም ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሞተ ።

፳፫ ፤ ዳግመኛም ፤ ለመለኮቱ ፡ የሚቻል ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፤ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ መነሣቱን ፡ እናምናለን ፡ ሞትን ፡ በሞቱ ፡ አጠፋው ፡ ከእኛም ፡ ሕማምን ፡ አጠፋ ፤ እንደ ፡ እርሱም ፡ ኢሥነሣን ፡ የማንታመም እንድንሆን ፤ ከጽድቅ ፡ እንዳንርቅ ፤ እንዳንለወጥም አደረገን ፤ የማታልፍ ፤ የማትፈጸም ፤ የተመሰገ ነች ፤ ሕይወትንም ፡ እንዲሰጠን ፡ ነገረን ።

፳፬ ፤ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ የጌታችን ፡ ንጹሕ ፡ ሥጋው ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፤ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ባሕርይ ፡ እንደተገኘ ፡ ወይም ፡ ነፍስ ፤ ዕውቀት ፡ እንደሌለው ወይም ፡ የማይታመም ፤ የማይሞት ፡ እንደሆነ ፤ የሚናገሩ ፡ ግን ፤ ይህን ፡ የሚናገሩ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ልብና ፤ አእምሮ ፡ እንዳሌላቸው ፡ ሰነፎች ፡ ይሆናሉ እኛም ፡ እነሱን ፡ እናርቃለን ፤ በጊዜውም ፡ ሁሉ ፡ የጽድቅ ፡ ጠላቶች ፡ የሆኑ ፡ ሐሰት ፡ ነገርን ፡ በከንቱ የሚከተሉ ፡ መናፍቃንን ፡ ሁሉ ፡ እናወግዛቸዋለን ።

ምዕራፍ ፡ ፻፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ የአንጾኪያና ፡ የስልቅ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ዮሐ ንስ ፡ የእስክንድርያ ፤ የግብጽና ፡ የተባባሪዎች ፡ አገ ሮች ፡ (ኖባና ፡ ፋስቆሎ) ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ሆነው ወደ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ከላከው ፡ መልእክት ፤ በመ ለኮት ፡ በአንዲት ፡ ኃይል ፡ በአንዲት ፡ ሥልጣን ፤ በአንዲት ፡ መንግሥት ፤ በአንዲት ፡ ፈቃድ ፡ በአንድ ውድ ፡ አንድ ፡ በሚሆኑ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ላይ እምነታችንን ፡ አድርገን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኢጋ ኾነት ፡ እንጀምራለን ፤ እነዚህም ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ የሚ ሆኑ ፡ ሦስቱ ፡ አካላት ፡ ሦስቱ ፡ ገጻት ፡ በአንዲት ፡ ስግደት ፡ ይሰገዳሉ ።

ዘዮሐንስ ፡ ፻፻ ።

፻ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ታኦንሎስ ፡ በእንተ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ እብል ፡ አንሰ ፡ ወእኪሞት ፡ ገሃደ ፡ በእንተ ፡ ባሕርይ ፡ ዘይትሌዓል ፡ እምዙሉ ፡ ወይሴ ባሕ ፡ ፈድፋደ ፡ በጽጹ ፡ መጠኮት ፡ እሱ ፡ እሙንቱ ፡ ፍጹማን ፡ መልክአ ፡ ዘበሕማን ፡ ያቁ ፡ አካላት ፡ ወያቁ ፡ ገጻት ፡ ዘውእቶሙ ፡ አብ ፡ ወወልድ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወኢይትበሀል ፡ ኮነ ፡ ካልኡ ፡ ድኅረ ፡ አሐዱ ፡ ወሣልሱ ፡ ድኅረ ፡ ካልኡ ፡ ይሴብሑ እምዙሉ ፡ አሐተ ፡ ስባሔ ፡ ወኢይትፈለጡ ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ እምነ ፡ ግብራት ፡ አብ ፡ ወላዴ ፡ ወልድ ፡ ውእቱ ፡ ወልድኒ ፡ ተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ ቅድመ ፡ እምቅድመ ፡ ዙሉ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማን ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ሀልው ፡ እምቅድመ ፡ ዙሉ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማን ፡ አብሰ ፡ ኢተወሰጊ ፡ ውእቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ወልድ ፡ ተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ወመንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ሠረጸ ፡ እምኔሁ ፡ ወሶበሂ ፡ ንቤ ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ኢተወልደ ፡ ወወልድሂ ፡ ተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ ወሀልው ፡ ምስሌሁ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስሂ ፡ ወዕለ ፡ እምኔሁ ፡ ኢተሐሊ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ የሐጽጽ ፡ እምአብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስሂ ፡ እምወልድ ፡ ከመ ፡ ልደት ፡ አበው ፡ አብርሃም ፡ ይሥሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ አላ ፡ ዕሩያን ፡ እሙንቱ ፡ በቅድምና ፡ ወበምልከና ፡ ወበፈጠረ ፡ ዙሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ወበዙሉ ፡ ግብር ፡ ዘይደሉ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፪ ፤ ወሶበሂ ፡ ንብል ፡ ፩ዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ ንብል ፡ በእንተ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሉ ፡ ሀልዋን ፡ እምቅድመ ፡ ዙሉ አዝማን ፡ ወመዋዕል ፡ ዘኢፍጡራን ፡ ወኢግቡራን ፡ ኢይትዌለጡ ፡ ወኢይትግመሩ ፡ ወኢያስተርእዩ ፡ አልቦሙ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ፡ ዐላውያን ፡ ዙሉ ፡ ጥንት ፡ ፈጣርያን ፡ ዙሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ከሀልያን ፡ ላዕለ ፡ ዙሉ ።

፫ ፤ ወሠራዕያን ፡ ዙሉ ፡ ፍጥረት ፡ እለ ፡ እሙራን ፡ በ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ወ፫ቱ ፡ ገጻት ፡ እንበለ ፡ ትድምርት ፡ ወእኁዛን ፡ በዕምረተ ፡ አሐቲ ፡ መለኮት ፡ እንበለ ፡ ተከፍሎ ፡ ወኢፍልጠት ፡ እንዘ ፡ ፩ዱ ፡ ፫ቱ ፡ ወእንዘ ፡ ፫ቱ ፡ ፩ዱ ፡ ተዋሕዶ ፡ በሥላሴ ፡ ወሥላሴ ፡ በተዋሕዶ ፡ እስመ ፡ ለአብሰ ፡ ዘበአማን ኢይቤላ ፡ መጻሕፍት ፡ ለግሙራ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተወልደ ፡ አላ ፡ ወላዴ ፡ ወልድ ፡ ውእቱ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፻፩ ።

፩ ፤ ታኦንሎስ ፤ ስለ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ እኔ ፡ ከሙስ ፡ የራቀ ፡ በአንድ ፡ መለኮት ፡ ፈጽሞ ፡ የሚመሰገን ፡ የባሕርይን ፡ ነገር ፡ ገልጬ ፡ እናገራለሁ ፤ በውነተኛ ፡ መልክ ፡ ፍጹማን ፡ የሚሆኑ ፡ ሦስቱ ፡ አካላት ሦስቱ ፡ ገጻት ፡ እንዚህ ፡ ናቸው ፤ እነዚህም ፡ አብ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ፤ ብሉ ፡ እንደ ተናገረ ፡ ሁለተኛው ፡ ከአንደኛው ፡ በኋላ ፤ ሦስተኛውም ፡ ከሁለተኛው ፡ በኋላ ፡ ተገኘ ፡ አይባልም ፤ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ አንዲት ፡ ምስጋናን ፡ ይመሰገናሉ፤ ከሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ አይለያዩም ፤ ወልድን የወለደ ፡ አብ ፡ ነው ፤ ወልድም ፡ ከቀን ፡ ከዘመን ከአስቀድሞ ፡ ከእርሱ ፡ ተወለደ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም፡ ከአብ ፡ ሠረጸ ።

፪ ፤ አብ ፡ ከቀን ፡ ከዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ነውና ወልድም ፡ ከቀን ፡ ከዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ነውና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከቀን ፡ ከዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ነውና ፤ አብ ፡ ያልተወለደ ፡ ነው፡ ብርሃን ፡ ከብርሃን ፡ እንዲገኝ ፡ ወልድ ፡ ከአብ ፡ ተገኘ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ ሠረጸ ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ አልተወለደም ፤ ወልድ ፡ ከአብ ፡ ተወለደ ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ በቅድምና ፡ የኖረ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ ሠረጸ ፡ ብለን ፡ ብንናገርም፤ እንደ ፡ አበው ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፤ እንደ ፡ ይስሐቅና ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ልደት ፡ ወልድ ፡ ከአብ ፡ ያንሳል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከወልድ ፡ ያንሳል ፡ ብለህ አታስብ ፡ በቀዳማዊነት ፡ በአገዛዝ ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመፍጠር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሚገባ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ።

፫ ፤ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ መለኮት ፡ ብንልም፡ ከቀን ፤ ከአዝማን ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፤ በአርምሞ ፡ በነቢብ ፡ የተፈጠሩ ፡ ስላይደሉ ፤ ስለ ፡ አብ ፡ ስለ ፡ ወልድ ፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንናገራለን፡ አይለወጡም ፤ አይወሰኑም ፤ አይታዩም ፤ ጥንት ፡ ፍጻሜ ፡ የለባቸውም ፤ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ የነበሩ ፡ ናቸው ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠሩ ፡ ናቸው ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ያለ ፡ መቀላቀል ፤ በሦስት ፡ አካላት ፡ በሦስት ፡ ገጻት ፡ የታወቁ ፤ ያለ ፡ መከፈል ፤ ያለ ፡ መለየት ፡ በእንዲት ፡ መለኮት ፡ አንድነት ፡ የጸኑ ፤ ፍጥረቱን፡ ሁሉ ፡ ወስነው ፡ የሚያኖሩ ፡ ናቸው ፤ አንድ ፡ ሲሆኑ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሲሆኑ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ አንድነት፡ በሦስትነት ፡ ሦስትነት ፡ በአንድነት ፤ አለ ፡ ስለ ፡ ግይ ለወጥ ፡ ስለ ፡ አብ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፤ ፈጽሞ ፡ አልተናገሩም ፤ ወልድን ፡ የወለደ ፡ እንደ ሆነ ፡ ተናገሩ ፡ እንጂ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፮ ።

፪ ፤ ወሎቱ ፡ ሥርዓተ ፡ አብና ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ወላዲ ወኢተወልደ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይሰመይ ፡ አበ ፡ ዘበአማን ፡ ወለወልድሂ ፡ ዓዲ ፡ ሎቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ወልድና ፡ ወበእንተዝ ፡ ይሰመይ ፡ ዘበአማን ፡ ወልደ ፡ ወኢይሰመይ ፡ አበ ፡ ወኢወላዴ ፡ አላ ፡ ተወላዲ ፡ ውእቱ ፡ ወለመንፈስ ፡ ቅዱስሂ ፡ ዓዲ ፡ ሎቱ ፡ ሥርዓተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ ወቦቱ ፡ አኀል ዘከመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወኢይሰመይ ፡ አበ ፡ ወኢወልደ ፡ አላ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ፡ ዘወፅአ ፡ እምአብ ።

፫ ፤ ወዘንተ ፡ ትምህርተ ፡ ተምህርነ ፡ ወለበውነ ፡ እም አበዊነ ፡ ቅዱሳን ፡ ለባሲያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢ ጎዝያን ፡ ምሥጢራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅድስት ፡ ንሕነሰ ፡ ምእመናን ፡ ንትአጎዝ ፡ ወንሄሉ በዘተምህርነ ፡ እምአበዊነ ፡ ተጋዳልያን ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ ወኢናንቀለቅል ፡ ለግሙራ ፡ ሀበ ፡ ካልእ ፡ ሃይማኖት ፡ በእንተ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወጸእሙ ናወግዝ ፡ ዙሎ ፡ መናፍቃን ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ወኢ ይትአመኑ ፡ በዘነበብነ ።

፮ ፤ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ወአልጸቀ ፡ ፍጻሜ ፡ መዋዕል ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ሠምረ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አብ ፡ ወፈነወ ፡ ወልዶ ፡ ፍቁሮ ፡ አድነነ ርእሶ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ወወረደ ፡ ኀቤነ ፡ እንዘ ፡ ልዑል ፡ ውእቱ ፡ አንደየ ፡ ርእሶ ፡ እንዘ ፡ ባዕል ፡ ወተትሕተ ፡ እንዘ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ወተርኢየ ፡ እንዘ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወፅአ ፡ እንዘ ፡ ኢይት ፈለጥ ፡ እምሕፅነ ፡ አቡሁ ፡ ሰማያትኒ ፡ ወምድር ፡ ምሉአን ፡ እምኔሁ ። ዘፍ ፡ ፲፰ ፡ ፲ ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፲፰ ፡ (፲፯) ፡ ፱ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፱—፲፩ ።

፱ ፤ ሠምረ ፡ ወወረደ ፡ ወጎደረ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በብሥራተ ፡ ገብርኤል ፡ መል አክ ፡ አመ ፡ ይቤላ ፡ ሰላም ፡ ለኪ ፡ አ ፡ ምልአተ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌኪ ፡ ቡርክት ፡ አንቲ ፡ አምአንስት ፡ ወናሁ ፡ ትፀንሲ ፡ ወትወልዲ ፡ ወልደ ወይሰመይ ፡ ስሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ወውእቱ ፡ ያድኅኖሙ ለሕዝቡ ፡ እምኃጢአቶሙ ፡ ቦኑ ፡ ይቤላ ፡ መልአክ ለድንግል ፡ ትወልዲ ፡ ወልደ ፡ በጀቱ ፡ ህላዌያት ፡ ሐሰ ፡ ወእለሰ ፡ ይከፍሉ ፡ ህላዌሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኀበ ፡ ጀቱ ፡ ህላዌያት ፡ አብዳን ፡ እሙንቱ ፡ ወር ገማን ፡ ሎቃ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፴፭ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፮ ።

፯ ፤ የአባትነት ፡ ስም ፤ ያባትነት ፡ ግብር ፡ ገንዘቡ ፡ ነው የወለደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አልተወለደምቁ ፤ ስለዚህ ፡ አባት ፡ የሌለው ፡ አባት ፡ ይባላል ፡ ዳግሞም ፡ ለወልድ ፡ የልጅነት ፡ ስም ፤ የልጅነት ፡ ግብር ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የሕይወትነት ፡ ስም ፤ የሕይወትነት ፡ ግብር ፡ ገንዘቡ ነው ፤ እንደ ፡ አብ ፡ እንደ ፡ ወልድ ፡ ያለ ፡ አካል ፡ አለው ፤ አብ ፡ ወይም ፡ ወልድ ፡ አይባልም ፤ ከአብ የሠረጸ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ።

፰ ፤ ይህንንም ፡ ትምህርት ፤ እግዚአብሔር ፡ ካደረባቸው ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተቀበለቻቸውን ፡ ምሥጢራትንም ፡ ወስነው ፡ ከያዙ ፡ አባቶቻችን ፡ ተምረን ፡ ዐውቀናል ፤ ያመን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ከቀና ፡ ከተጋዳልያን ፡ አባቶቻችን ፡ በተማርነው ፡ ትምህርት ፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፤ ስለ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ካመነው ፡ እምነት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ አንናወጥም ፡ በተናገርነው ፡ የማያምኑ ፡ መናፍቃንን ፡ ሁሉ ፡ እናወግዛለን ፤ እንጂ ።

፱ ፤ የዘመኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የሚወደውን ፡ ልጁን ፡ በፈቃዱ ፡ ላከ ፡ ልዑል ፡ ባሕርይ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ከብር ፡ የማይሻ ፡ ሲሆን ፡ ክብር ፡ የሚሻ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ የከብር ፡ ባለቤትም ፡ ሲሆን ፡ ተዋረደ ፡ አምላክ ፡ ሲሆን ፡ በሥጋ ፡ ታየ ተገለጠ ፤ ከአባቱ ፡ አንድነት ፡ ሳይለይ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጣ ፡ ሰማይም ፡ ምድርም ፡ በእርሱ ፡ ተመልተዋል ። ዘፍ ፡ ፲፰ ፡ ፲ ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፲፰ ፡ (፲፯) ፡ ፱ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፱—፲፩

፱ ፤ በመልአኩ ፡ በገብርኤል ፡ ቃል ፡ ጸጋ ፡ ክብርን ። የተመላሽ ፡ ድንግል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሥጋሽ ፡ ሥጋ ፤ ከነፍስሽ ፡ ነፍስ ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ይሆናልና ክብር ፡ ይገባሻል ፤ ከሴቶች ፡ ተለይተሽ ፡ የከበርሽ ነሽ ፤ እነሆ ፡ ትፀንሻለሽ ፤ ወልድንም ፡ ትወልጃለሽ፤ ስሙም ፡ ኢየሱስ ፡ ይባላል ፤ እሱም ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ያድናቸዋል ፡ ባለት ፡ ጊዜ ፡ በፈቃዱ ፡ ወርዶ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕፀን ፡ አደረ ፤በውኑ ፡ መልአክ ፡ ለድንግል ፡ በሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ትወልጃለሽ ፡ አላትን ፤ አላላትም ፡ የክርስቶስን ፡ ባሕርይ ወደሁለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚከፍሉ ፡ ግን ፡ ዓላዋቆች፡ የተረገሙ ፡ ናቸው ። ሎቃ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፴፭ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፯ ።

፩ ፤ ወናሁ ፡ ዙሉሙ ፡ መምህራን ፡ ይትእመኑ ፡ ከመ ክርስቶስ ፡ ዘተሠገወ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ አካል ፡ ወ፩ዱ ፡ ገጽ ፡ እምፍቱ ፡ ገጸት ፡ እለ ፡ ዕሩያን ፡ በመለኮት ፡ ወከመዝ ፡ ዓዲ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሊድስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘሮምያ ፡ በእንተ ፡ ተዋሕዶቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወሶበሂ ፡ ንሰምዮ ፡ ሰብእ አልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘይክሕድ ፡ ህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ዘይትዋሐድ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ወሶበሂ ፡ ንሰምዮ ፡ ገብረ በእንተ ፡ ሥጋ ፡ ዘለብሶ ፡ አልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘይክሕድ ፡ ህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወመንግሥቶ ፡ ዘለዓለም ፡ ወኢይትከፈል ፡ በምግባር ፡ ወኢበስም ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ እምነ ፡ ፪ቱ ፡ ጠባይዕ ፡ ፍጹማን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ኢይትበህል ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ በስምኒ ፡ ወበህላዌኒ ፡ ወሶበሂ ፡ ይሰመይ ፡ ሥጋ ፡ አኮ ፡ ዘትትፈለጥ ፡ እምኔሁ ፡ ነፍስ ፡ ወሶበሂ ፡ ይሰመይ ፡ ዙሉንታሁ ፡ ነፍስ ፡ አኮ ፡ ዘይትፈለጥ ፡ እምኔሁ ፡ ሥጋ ፡ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለኮቱ ፡ ለአምላክነ ፡ ምስለ ትስብእቱ ፡ ኢይትበህል ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፩ና ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፭፬ ።

፪ ፤ ወከማሁ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘአለ ፡ እስክንድርያ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ሃይማኖትነ ፡ ርትዕት ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ነሣእናሃ ፡ ወተምህርናሃ እምአበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ ወእርትዕዋ ፡ አበው ፡ ወከመትዋ ፡ እመጽሐፈ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ወእምነ ቢያትሂ ፡ ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይቤ ፡ ፈኑ ፡ ቃለከ ፡ ወጽድቀከ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይቤ ፡ ናሁ ፡ ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ ፡ ወይሰመይ ፡ ስሙ ፡ አማኑኤል ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌነ ፡ ወምንትኑ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ይትወለድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሥጋ ፡ ኢሳ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፵፫ ፡ (፵፪) ፡ ፫ ፡ ፻፯ ፡ (፻፮) ፡ ፳ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፫ ፤ ወበካልእኒ ፡ ገጸ ፡ መካን ፡ ይብል ፡ አመቦ ፡ እምነ ፡ ምእመናን ፡ ዘኢየአምን ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘአስተርአየ ፡ እግርያም ፡ ድንግል ፡ ወኮነ ሰብአ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ሰማያዊ ፡ ዘበአማን ወቃልሂ ፡ ዘውእቱ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ተሰብአ ፡ እምዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ወጉዘ ፡ ለይኩን ።

፬ ፤ ወበካልእኒ ፡ ገጸ ፡ መካን ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ወልደ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ቦቱ ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ቃልሰ ፡ ዘእምአብ ፡ ተወልደ ፡ ቅድመ ፡ እምቅድመ ፡ ዙሉ ፡ አዝማን ፡ እመልዕልተ ፡ ዙሉ ፡ ንባብ ፡ ወኢንክል ፡ አብጽሖተ ፡ ፍካሬሁ ፡ በንባብ ፡ ወበልቡና ፡ እስመ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ እምቅድመ ፡ ዙሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ዘመልዕልተ ፡ ወዘመትሕተ ፡ ወለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ፈጣሪሆሙ ፡ ወባሕቱ ለሊሁ ፡ ሠምረ ፡ በፈቃዱ ፡ ወአስተርአየ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፯ ።

፩ ፤ እነሆ ፡፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ክርስቶስ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ በመለኮት ፡ አንድ ከሚሆኑ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላትም ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እንደሆነ ፡ ያምናሉ ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ የሮማ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሊድስ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ተዋሕዶ ፤ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብንልም ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ የተዋሐደ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱን ፡ የሚክድ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ ሥጋን ፡ ስለ ፡ ተዋሐደ ፡ አገለገለ ፡ ብንለውም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱን ፤ የዘላለም ፡ መንግሥቱን የሚክድ ፡ ማንም ፡ የለም ፡ ፍጹማን ፡ ከሚሆኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ጠባዕያት ፡ (ከነፍስ ፡ ከሥጋ) ፡ የተገኘ ፡ ሰው፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ በአንድ ፡ ስም ፡ ይጠራል፡ እንጂ ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ እንዳይባል ፤ በስም ፤ በግብር ፡ አይከፈልም ፤ ሥጋ ፡ ተብሎ ፡ በተጠራ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ከርሱ ፡ የምትለይ ፡ አይደለችም ፤ ሁሉንተናው ፡ ነፍስ ፡ ተብሎ ፡ በተጠራ ፡ ጊዜም፡ ሥጋ ፡ ከእሱ ፡ የሚለይ ፡ አይደለም ፤ የፈጣሪያቸንም መለኮቱ ፡ ከሥጋው ፡ የተዋሐደው ፡ ተዋሕዶ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ግን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ አካል ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አይባልም ፡ ብሏል ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፩ና ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፭፬ ።

፪ ፤ እንዲሁ ፤ የእስክንድርያ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ አትናቴዎስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ከአባቶቻችን ፡ ከሐዋርያት፡ የተማርናት ፤ ከሊቃውንትም ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ፡ ከነቢያትም ፡ መጽሐፍ ፡ እግኝተው ፡ ገልጸው ፡ ያስረዱአት ፡ ሃይማኖታችንስ ፡ የቀናች ፡ ናት ፤ ከእነሱም ፡ አቤቱ ፡ ቃልህን ፡ ጽድቅህን ፡ ላክ ፡ ያሉ፡አለ፡ ከእነዚህም ፡ እነሆ ፡ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም ፡ ትወልዳለች ፤ ስሙም ፡ አማኑኤል ፡ ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ ማለት ፡ ነው ፡ ያለ ፡ አለ ፤ የዚህ ፡ ትርጓሜው ፡ ምድን ነው ? እግዚአብሔር ፡ በሥጋ ፡ ይወለዳል ፡ ማለት) ነው ፤ እንጂ ። ኢሳ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፵፫ ፡ (፵፪) ፡ ፫ ። ፻፯ ፡ (፻፮) ፡ ፳ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፫ ፤ በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሆኖ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ተወልዶ ፡ የታየ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በውነት ፡ የሰማያዊ ፡ የአብ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ቃልም ፡ ከዳዊት ወገን ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ የማያምን ፡ ሰው ፡ ቢኖር፡ ውጉዝ ፡ ይሁን ።

፬ ፤ በሌላም ፡ አንቀጽ ፤ በእርሱ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ የአዳም ልጆች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፤ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይናገራል ፤ ቃል ፡ ግን ፤ ከዘመን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከአብ ፡ የተወለደው ፡ ልደት ፡ ከመነገር ፡ ሁሉ ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ ምሥጢሩን ፡ በልቡና ፡ መርምረን ፡ መናገር ፡ አይቻለንም ፤ በሰማይ ፡ በምድር ፡ ካሉ ፍጥረታት ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ነውና ፡ ፈጣሪያቸውም ፡ እርሱ ፡ ነውና ፤ ነገር ፡ ግን፡ እርሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተገለጠ

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፯ ።

፲፬ ፤ ወከማሁ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ በእንተ ፡ ሀላዌያት ፡ ፪ቱ ፡ ኢፍሉጣን ፡ እሙንቱ ፡ አላ ፡ ስንዕዋን ወዕሩያን ፡ በስባሔ ፡ ወአልቦሙ ፡ ፍልጠት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ለግሙራ ፡ ወለእመኒ ፡ ተብህለ ፡ ኅደረ ፡ ፩ዱ ፡ በካልኡ ፡ ከመ ፡ ምንትኒ ፤ ግብር ፡ ኢይደሉ ፡ ይፍልጥዎ ፡ ኅበ ፡ ፪ቱ ፡ እስመ ለሊሁ ፡ ተጋብአ ፡ በተዋሕዶተ ፡ ፩ዱ ፡ ከዊን ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

፲፭ ፤ ወከመዝ ፡ ዓዲ ፡ ያረብሐነ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጠቢብ ፡ በቃለ ፡ ምህሮሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ዘአፍአ ፡ ይትዌለጥ ፡ ወባሕቱ ፡ ብእሲ ፡ እንተ ፡ ውስጥ ፡ ይትሔደስ ፡ ዕለተ ፡ እምዕለት ፡ ወበ ብሂሎቱሰ ፡ ብእሲ ፡ ዘውስጥ ፡ ዘኀዱር ፡ በዘአፍአዊ ፡ ነበበ ፡ በዝንቱ ፡ ጽድቀ ፡ ወባሕቱ ፡ ረሰዮ ፡ ፩ደ ፡ ወኢከፈሎ ፡ ኅበ ፡ ፪ቱ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።

፲፮ ፤ ወቅዱስሂ ፡ ዮሐንስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘቊስጥንጥ ንያ ፡ ይቤ ፡ ኅደረ ፡ ላዕለ ፡ ድንግል ፡ ፀሐየ ፡ ጽድቅ ዘበአማን ፡ ዘኢይትገመር ፡ ወኢይትዌለጥ ፡ ወኢ ንትኅሠሥ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ከሀሊ ፡ ዘከመ ፡ ፈቀደ ፡ ሁሎ ፡ ይገብር ፡ ወኢይሰዓኖ ፡ ምንትኒ ፡ ግብር ፡ ወለሊሁ ፡ በፈቃዱ ወረደ ፡ ወኢድኅነ ፡ ሁሎ ፡ ፍጥረቶ ፡ እንዘ ፡ አም ላክ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወሐመ ፡ በሕማመ ፡ ዚአነ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢተወለጠ ፡ መለኮት ፡ ለከ ዊነ ፡ ትስብእት ፡ ወትስብእትሂ ፡ ለከዊነ ፡ መለ ኮት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሀሎ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወውእቱሂ ፡ ይሄሉ ፡ በከመ ኮነ ፡ ቀዲሙ ፡ ወኢይትዌለጥ ፡ ለብሰ ፡ ሥጋ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይቤዝወነ ፡ ወያንሥአነ ፡ እምድቀትነ ፡ ዘወደቅነ ፡ ባቲ ፡ ወበጸሐነ ፡ ለሐ ጕል ፡ ወለሙስና ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፯ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፫ ።

፲፯ ፤ ወቅዱስሂ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘለእስክ ንድርያ ፡ ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ቃል ፡ ሥምረ ፡ ይኩን ፡ ሰብአ ፡ ዘእን በለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ወኅደረ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ድንግል ፡ በከመ ፡ ይቤላ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመጽእ ፡ ላዕሌኪ ፡ ወኀይለ ፡ ልዑል፡ የኀድር፡ ውስተ፡ ከርሥኪ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፭

፲፰ ፤ ወኅርኅርዮስኒ ፡ ቴዎንሎስ ፡ ይቤ ፡ እመቦ ፡ ዘኢየ አምን ፡ ከመ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ይእቲ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ዘበ አማን ፡ ወኀዘ ፡ ለይኩን ፡ ወርሑቅ ፡ ውእቱ ፡ እም እግዚአብሔር ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፯ ።

፲፱ ፤ እንዲሁም ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ባሕር ያት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የተለያዩ ፡ አይደሉም ፤ አንድ ናቸው ፡ እንጂ ፤ በክብርም ፡ ልዩነት ፡ የለባቸውም፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላም ፡ ፈጽሞ ፡ መለያየት ፡ የለባቸ ውም ፡ አለ ፤ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ አደረ ፤ (ቃል ፡ ሥጋ ሆነ ፡ በእኛም ፡ አደረ) ፡ ቢባልም ፡ እንደ ፡ ማናቸ ውም ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ሊከፍሉት ፡ አይገባም፤ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በመ ሆን ፡ አንድ ፡ ሆናአልና ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

፳ ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ወዋቂው ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ወንጌልን ፡ በሚያስተምርበት ፡ ጊዜ ፤ በአፍአ ፡ ያለ ሰውነታችን ፡ በሕማም ፤ በሞት ፡ ይለወጣል ፤ውሳ ጣዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ግን ፤ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ ይታ ደሳል ፡ ብሎ ፡ ያስረዳናል ፤ በአፍአዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ያደረው ፡ ውሳጣዊ ፡ ሰውነታችን ፡ በማለቱ ፡ በዚህ እውነትን ፡ ተናገረ ፤ አንድ ፡ አደረገው ፡ እንጂ ። ወደሁለት ፡ አልከፈለውም ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ።

፳፩ ፤ የቊስጥንጥንያ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ የማይወሰን ፡ የማይለወጥ ፤ የታመነ ፡ እውነተኛ ፡ ፀሐይ ፡ በድንግል ፡ ማኅፀን ፡ አደረ ፡ ግን ፡ እንዴት፡ እንደ ፡ አደረ ፡ አንመራመር ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ሁሉን ፡ ይሠራልና፤ ምንም ፡ አይሳነውምና ፡ እሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ወርዶ ፡ ፍጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ አዳነ ፤ አምላክ ፡ ሲሆን ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ የእኛንም ፡ ሕማም ፡ ታመመ ፤ ስለዚህም ፤ መለኮት ፡ ሥጋን ፡ ወደ ፡ መሆን ፤ ሥጋም ፡ መለኮትን ወደ ፡ መሆን ፡ አልተለወጠም ፤ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነውና ፡ እሱ ፡ አሰቀ ድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ በባሕርዩ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፤ አይለወጥም ፤ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ለጥፋትና ፡ ለሞትም ፡ ደርሰንባት ፤ ተይዘንባት ፡ ከነበረችው ፡ ከኃጢአታችን ፡ ፍዳ ፡ ያወጣን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ሰው ፡ ሆነ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፫ ።

፳፪ ፤ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያለ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ሰው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፤ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድርብሻል ፤ ኀይለ ፡ ልዑል ፡ ወል ድም ፡ በማሕፀንሽ ፡ ያድራል ፡ ብሎ ፡ መልአኩ ፡ ገብርኤል ፡ እንደ ፡ ነገራት ፤ በድንግል ፡ ማሕፀን ፡ አደረ ፡ አለ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ።

፳፫ ፤ አንድነትን ፡ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎርዮስም፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በው ነት ፡ እምላክ ፡ ቃልን ፡ የወለደች ፡ እንደሆነች ፡ የማ ያምን ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ፡ ከእግዚ አብሔርም ፡ የራቀ ፡ ነው ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፯ ።

፲፱ ፤ ወነገርነሮሶስ ኂ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘኑሲስ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ነአምን ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ጎይሉ ፡ ውእቱ ለእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወጥበቡ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ወኢይትቄለጥ ፡ ወሶበሂ ፡ ጎደረ ፡ በዘይ ትቄለጥ ፡ ወይትመየጥ ፡ ወይማስን ፡ ውእቱሰ ፡ ኢተወለጠ ፡ ወኢተመይጠ ፡ ኢረስሐ ፡ ወኢማ ሰነ ፡ አላ ፡ አንጽሖ ፡ ለዘይረስሕ ፡ ወረሰዮ ፡ ዘኢ ይማስን ፡

፳ ፤ ወቅዱስሂ ፡ ቄርሎስ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ጥበብ ፡ ተወ ልደ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ኢይትቄለጥ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወተመሰለን ፡ በሥሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ፡ ኃጢአት ፡ በሕቲታ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ሰማያዊ ፡ ዘበአማን ፡ ወበ እንተ ፡ ሕማማቲሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ ይቤሉ ፡ አበዊነ ፡ ቅዱሳን ፡ ወእምኔ ሆሙ ፡ ነርነርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለክት ፡ ይቤ ፡ በድ ርሳኑ ፡ ዘኮኖነረ ፡ በእጉሉ ፡ ሕማማቲሁ ፡ ለእግዚ እነ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢትትዐቀፍ ፡ በሕሊናከ ፡ ሶበ፡ ትሰምዕ ፡ ድካሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሕማማቲሁ ወሞቶ ፡ ወኢትትሀወክ ፡ ዘከመ ፡ አንተ ፡ ትፈቅድ ፡ ትኩን ፡ ጽዱቀ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወባ ሕቱ ፡ እንበለ ፡ ምክንያት ፡ ብላዕ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክር ፍስቶስ ፡ ወስተይ ፡ ደሞ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕቅፍት ፡ እመ ፡ ኮንከ ፡ ትፈቅድ ፡ ወትፈቱ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለ ዓለም ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ኗ፱ —፴ ።

፳፩ ፤ ወዓዲ ፡ ነርነርዮስ ፡ ገባሬ ፡ መንክራት ፡ ይብል ፡ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ካልእ ፡ ውእቱ ፡ ዘሐመ ፡ ወካልኡ ፡ ውእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡ ወኢይትአመን ፡ ከመ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘኢየሐምም ፡ በመ ለኮቱ ፡ ወሐመ ፡ በሥጋ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ወቅ ዱስኒ ፡ ባስልዮስ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ አምላክ ፡ ኵሉ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ዘከመ ፡ ሞትን ፡ ወወሀበ ፡ ሕይወተ ለኵሉ ፡ ስብእ ፡ ወቅዱስሂ ፡ ሚሊጠን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘቲካ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ዘኅረራ ፡ ለምድር ፡ ተሰቅለ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወሞተ ፡ በእን ቲአነ ፡ ከመ ፡ ያሕይወነ ።

፳፪ ፤ ወቴዎኅሎስሂ ፡ ይቤ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ይሠገው ፡ ወይሕምም ፡ ወይሙት ፡ በእን ቲአነ ፡ ከመ ፡ ንሕየው ፡ ንሕነ ፡ በሞተ ፡ ዚአሁ ፡ ወይደልዎሙኬ ፡ ዓዲ ፡ ለኵሎሙ ፡ ፍጡራን ፡ ከመ ፡ ይሕምሙ ፡ ወይሙቱ ፡ ምስለ ፡ ፈጣሪሆሙ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመቦ ፡ ዘኢየአምን ፡ ወኢይሰ ግድ ፡ በዘተሰቅለ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፱ ።

፲፱ ፤ የኑሲስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ነርነርዮስም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ እኛስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ጥበቡ ፡ ኃይሉ ፡ ነውና ፡ እሱ ፡ ፈጽሞ ፡ እን ደማይለወጥ ፡ እናምናለን ፤ በሚለወጥ ፤ በሚፈርስ በሚበሰብስ ፡ ሥጋ ፡ ቢያደርም ፡ እሱስ ፡ ባሕርዩን አልለቀቀም ፡ አልተለወጠም ፤ ኃጢአት ፡ አልተገ ኘበትም ፡ ሙሰኖ ፡ መቃብር ፡ አላገኘውም ፤ ኃጢ አት ፡ የሚስማማውን ፡ አነጻው ፤ የማይለወጥም ፡ አደረገው ፡ እንጂ ።

፳ ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡ ጥበብ ፡ ቃል ፡ ከባሕርየ ፡ መለ ኮቱ ፡ ሳይለወጥ ፡ በሥጋ ፡ ተወለደ ፤ እርሱ ፡ ሰማ ያዊ ፡ የአብ ፡ ልጅ ፡ ሲሆን፡ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር በሥራው፡ ሁሉ ፡ መሰለን ፡ አለ ፤ የጌታችን፡የኢየሱስ ክርስቶስን ፡ የሕማሙን ፡ ነገር ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶቻ ችን ፡ ተናግረዋል ፤ ከእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ አንድኑትን ምስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ነርነርዮስ ፡ የጌታችን ፡ የክ ርሰቶስን ፡ የሕማሙን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ ድር ሳኑ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ድካሙን ፡ ሕማሙን ፡ ሞቱን ፡ በሰማህ ፡ ጊዜ ፡ በልቡናህ ፡ አትጠራጠር፤ በእግዚአብሔር ፡ዘንድም ፡ ጸድቅ ፡ ልትሆን ፡ ሽተህ አትታወክ ፤ ግን ፡ የማታልፍ ፡ ሕይወትን ፡ (የመንግ ሥተ ፡ ሰማያትን) ፡ የምትሻ ፡ ከሆንክ ፡ ምክንያት ሳታበዛ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋውን ፡ ብላ ፤ ሳትጠራ ጠርም ፡ ደሙን ፡ ጠጣ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ኗ፱—፴ ።

፳፩ ፤ ዳግመኛም ፤ ተአምራትን ፡ ያደረገ ፡ ቅዱስ ፡ ነርነር ዮስ ፡ የታመመው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ የማይታመመው፡ ሌላ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ በመለኮቱ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የሌለ በት ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ የማያምን ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይሁን ፡ ይላል ፡ ቅዱስ ባስልዮስም ፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሞትን ፡ በሥጋ ፡ ሞቶ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ሕይወትን ሰጠ ፡ ብሏል ፡ የቲካ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ሚል ጦንም ፡ ምድርን ፡ የፈጠራት ፡ በመስቀል ፡ ላይ ተሰቀለ ፡ ያድነን ፡ ዘንድም ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

፳፪ ፤ ቴዎኅሎስም ፡ እኛ ፡ በእርሱ ፡ ሞት ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሊታ መም ፡ ሊሞት ፡ ወደደ ፡ አለ ፤ እንዲሁ ፡ ፍጡራንም ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ሊታመሙ ፡ ሊሞቱ፡ ይገባቸዋል ፡ አለ ፡ ዳግመኛም ፡ በተሰቀለው ፡ የማያ ምን ፤ የማይሰግድ ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይሁን ፡ አለ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፯ ።

፩፻ ፤ ወዮሐንስኒ ፡ አፈወርቅ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ቡሩክ ፡ ፈቀደ ፡ ወሠምረ ፡ ከመ ፡ ይኩን፡ ሰብእ ፡ ይሕምም ፡ ወይሰቀል ፡ ወይሙት ፡ ወይ ትንሣእ ፡ ወናሁ ፡ ተከሥተ ፡ ለን ፡ ስምዓ ፡ ሃይማ ኖተ ፡ ርትዕት ፡ በብሥራቱ ፡ ለገብርኤል ፡ መልአክ ዘአብሠራ ፡ ለድንግል ፡ ወበዘተነበዩ ፡ ነቢያት ፡ ወሰበኩ ፡ ሐዋርያት ፡ ወአግህድዎ ፡ መምህራን ፡ እለ ፡ ዘከርን ፡ አስማቲሆሙ ፡ በውስተ ፡ መጽሐ ፍን ፡ ዛቲ ፡ እስመ ፡ መፍቅድነሰ ፡ ተሰፍዕዎተ ፡ ጸቱ ፡ መናብርት ፡ ዘውእቶሙ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወመንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወረደቁዶስ ፡ ተሰናዕዎተ ፡ እሉ ፡ አኃው ፡ መሲሐውያን ፡ እለ ፡ አጽንዑ ፡ ሃይማኖተ ፡ ርትዕተ ።

፩፻፩ ፤ ወንትዌከፍ ፡ ዓዲ ፡ ቃለ ፡ አበው ፡ እለ ፡ ተጋደሉ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ዘንተ ፡ ፫ተ ፡ ጉባኤያተ ፡ እሙራነ ፡ እለ ፡ አጽንዑ፡ ሃይማኖተ ፡ ርትዕተ ፡ ወጽድቅተ ፡ ወጸዱ ፡ ጉባኤ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘኮነ ፡ በሀገረ ፡ ኒቅያ ፡ እለ ፡ ተጋብኡ ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ወአውገዝዎ ፡ ለአርዮስ ፡ ዕልው ወርጉም ፡ ወአውደቅዎ ፡ ወካልእሂ ፡ ጉባኤ ፡ እለ ፡ ተጋብኡ ፡ በሀገረ ፡ ቊስጥንጥንያ ፡ ወአውደቅዎ ፡ ለመቅዶንዮስ ፡ ዕልው ፡ ዘፀረፈ ፡ ላዕለ ፡ መንፈስ ቅዱስ ፡ ወሣልስሂ ፡ ጉባኤ ፡ ዘተጋብኡ ፡ በሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ምስለ ፡ ብፁዕ ፡ ወወቢይ ፡ ቄርሎስ ፡ ወአ ውደቅዎሙ ፡ ለንስጥሮስ ፡ ወለዙሉሙ ፡ ዐላውያን።

፩፻፪ ፤ ወዓዲ ፡ ንትዌከፍ ፡ አበወ ፡ ክቡራን ፡ ወትሩፋን ፡ እለ ፡ ተጋደሉ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ብፁዕ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ ሳት ፡ ዘለእስክንድርያ ፡ ወጴጥሮስኒ ፡ ዘተከለለ ፡ በስምዕ ፡ ወቴዎፍሎስ ፡ ዘአብርሀ ፡ ዓለመ ፡ ወቄ ርሎስ ፡ መምህር ፡ ዓቢይ ፡ ወክቡር ፡ ወጢሞቴ ዎስ ፡ ዐቢይ ፡ ወዲዮስቆሮስ ፡ ተጋዳሊ ፡ ለአጽንዖ ሃይማኖት ፡ ወአቡሊዲስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ወቅዱስ ፡ ባስልዮስ ።

፩፻፫ ፤ ወጎርጎርዮስ ፡ ገባሬ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ወጎርጎርዮስ ፡ ቴዎሎስ ፡ ወጎርጎርዮስ ፡ ዘኑሲስ፡ ወቅዱስ ፡ ማሪ ፡ ኤፍሬም ፡ ወቅዱስ ፡ ማር ፡ ሳዊ ሮስ ፡ መምህር ፡ ዐቢይ ፡ ወቅዱስ ፡ ማር ፡ ያዕቆብ ፡ ወዙሉ ፡ ዘጎብረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወተሰነዐወ ፡ ላቊለ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ አጽንሑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ቅድስት ፡ ዘእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ እንተ ፡ ተሣ የጣ ፡ በደሙ ፡ ክቡር ፡ በከመ ፡ ንቤ ፡ ለእሉ ፡ ዙሉሙ ፡ አበው ፡ ንጹሐን ፡ ንስግዕ ፡ ቃላቲሆሙ፡ ጽድቅተ ፡ ወንትሰ፡አሠሮሙ ፡ ብርሀተ ፡ ወቅድስተ

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፸ ።

፩፻፩ ፤ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፡ ምስጉን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፤ ሊታመም ፤ ሊሰቀል ፤ ሊሞት ፤ ሊነሣ ወደደ ፡ አለ ፤ የቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ምስክርን ፡ መል እኩ ፡ ገብርኤል፡ ለድንግል ፡ በአበሠራት፡ ብሥራት ነቢያት ፡ በተናገሩት ፡ ትንቢት ፤ ሐዋርያትም ፡ በአስተማሩት ፡ ትምህርት ፤ እነሆ ፡ ተረዳን ፤ ስማ ቸውን ፡ በዚህች ፡ መጽሐፍችን ፡ ያነማነው ፡ መም ህራንም ፡ ገልጸውታል ፤ ፈቃዳችንስ ፡ የሁለቱ ፡ መናብርት ፡ አንድነት ፡ ነው ፤ እነዚህስ ፡ የጴጥሮስ፡ መንበርና ፡ የማርቆስ ፡ መንበር ፡ ናቸው ፤ ይልቁ ንም ፡ የቀናች ፡ ሃይማኖት ን ፡ ያጸኑ ፡ የእነዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ወንድማማች ፡ አንድነት ፡ ነው ።

፩፻፪ ፤ ዳግመኛም ፤ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ መከራን ፡ የተቀበሉ ፡ የአበውን ፡ ትምህርት ፡ እንቀበላለን ፤ ይልቁንም ፡ የተረዳች ፤ የቀናች ፡ ሃይማኖትን ፡ ያጸኑ የታወቁትን ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ ጉባኤ ፡ እንቀበላ ለን ፡ ከእነዚህም ፡ አንዱ ፡ በኒቅያ ፡ አገር ፡ የተደረ ገው ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ሊቈጡንት፡ ከሓዲ ፡ ርጉም ፡ አርዮስን ፡ አውግዘው ፡ የሰዩበት ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፤ ሁለተኛውም ፡ በቊስጥንጥንያ ፡ ተሰ ብስበው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የካደ ፡ መናፍቅ፡ መቅዶንዮስን ፡ አውግዘው ፡ የለዩበት ፡ ነው ፤ ሦስተ ኛውም ፡ ከደገኛው ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ጋር ፡ በኤ ፌሶን ፡ ተሰብስበው ፡ ንስጥሮስንና ፡ መናፍቃንንም ፡ ሁሉ ፡ አውግዘው ፡ የለዩበት ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

፩፻፫ ፤ ዳግመኛ ፤ ስለሃይማኖት ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ ፍጹ ማን ፡ ክቡራን ፡ አበውን ፡ እንቀበላለን ፤ ከነዚህም የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አትናቴዎስ በሰማዕትነት ፡ የሞተ ፡ ጴጥሮስ ፤ በትምህርቱ ፡ ዓለ ምን ፡ ወሞቂ ፡ ያደረገ ፡ ቴዎፍሎስ ፤ ደገኛው ፡ መም ህር ፡ ቄርሎስ ፡ ደገኛው ፡ ጢሞቴዎስ ፤ የቀናች ፡ ሃይማኖትን ፡ ለማጽናት ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ ዲዮ ስቆሮስ ፡ የሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊድስና ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ናቸው ።

፩፻፬ ፤ ብዙ ፡ ተአምራትንና ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ሥራን ፡ ያደ ረገ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ቴዎሎስ ፡ የተባለ ፡ ጎርጎርዮስ ፤ የኑሲስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የእግዚአብ ሔር ፤ አገልጋይ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ፡ ደገኛው ፡ መምህር ፡ ሳዊሮስ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብና ፡ በቀናች፡ ሃይማኖት ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ የተባ በረ ፡ ሁሉ ፡ ነው ፤ በክበረ ፡ ደሙ ፡ የዋጀችን ፡ በጌታ ችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያመነች ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ያጸኑ ፡ ናቸው ፤ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ የእነዚህን ፡ የንጹሐን ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ ሁሉ ፡ የተረዳች ፡ ትምህርታቸውን ፡ እን ስማ ፤ የከበረች፡ የታወቀች፡ ግብራቸውንም ፡እንያዝ

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፯ ፡ ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፭

ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡

፳፯ ፤ እመልእከተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ጎበ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለእስክንድርያ ፡ እውሥአተ ፡ መልእክቱ ፡ ጎቤሁ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ አምላክ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወረደ ፡ እምሰማይ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል፡ በእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወተሠገወ ፡ እምእግዝእትነ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወንጽሕት ፡ ዘእን በለ ፡ ውሳጤ ፡ ወነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ ሥጋ ፡ ዘበቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወከነ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ ዘበአማን ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወሚጠት ፡

፳፰ ፤ ወሐመ ፡ በሕማም ፡ ነ ፡ ወፈጸመ ፡ ሞቶ ፡ ዘዚአነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ አከ ፡ ዘንቤ ፡ በሕሊና ፡ ዘይስሕት ፡ ወይትዐቀፍ ፡ አላ ፡ ነአምን ፡ እሙነ ፡ በከመ ፡ ጸሐፈ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወነደረ ላዕሌነ ፡ ወዘንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሶበ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ፡ ኮነ ፡ ምስለ ፡ ፅጌለ ፡ እመሕያው ፡ ለእመ ንዮ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ቀፈጽሞ ፡ ሥርዓተ ፡ መድኃ ኒቶሙ ፡ እንዘ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ እምኔሁ ፡ ዘውእ ቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትሰብእት ፡

፳፱ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንብል ፡ ፩ዱ ፡ እግዚእ ፡ ወ፩ዱ መሲሕ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካል ፡ ወ፩ዱ ፡ ገጽ ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተሠገወ

፴ ፤ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ እምንትነ ፡ ዘከሠትናሁ ፡ ለከ ፡ አ ፡ ቅዱሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አ ፡ እጐ ፡ ፍቁር ፡ ዘስን ዕው ፡ በሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ወበሕሊና ፡ ዘሠረቀ ፡ በትምህርት ፡ ሐዋርያዊት ፡ ወሥርው ፡ ሠናይ ፡ እንተ ፡ ዘመድኃኒት ፡ ወመራሔ ፡ ሃይማኖት ፡ ፍጽ ምት ፡ ወምሥጥርት ፡ ወተወልዶ ፡ ልደተ ፡ ሠና ይት ፡ እንተ ፡ ታሜርየነ ፡ ወታስተዋሕደነ ፡ በም ሥጢረ ፡ አምልኮ ፡ ፍጽምት ፡ ወክብርት ፡ ወሐ መር ፡ ህድእት ፡ እንተ ፡ ኢትትሀወክ ፡ እምኀደ ፡ ማዕበላት ፡ ወታበጽሕ ፡ ውስተ ፡ መርሰ ፡ መድኃ ኒት ፡ ዘምልእት ፡ ፍሥሓ ፡ ወተድላ ፡ ወዕንቊ ፡ ክብርት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ነውር ፡ ዘብዙኅ ፡ ሚጣ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስከ ፡ ለዓ ለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡

ምዕራፍ ፡ ፪፭ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡

፩ ፤ እመልእከተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአቡነ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለእስክንድርያ ፡ ወግብጽ ፡ ጎበ ፡ አቡነ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአ ንጾኪያ ፡ አውሥአተ ፡ መልእክት ፡ ዘተፈነወ ፡ እምኀቤሁ ፡ ነአምን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወወ ልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ወ፫ቱ ፡ ገጻት ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወአሐቲ ፡ ክብር ፡ ወአሐቲ ፡ መንግሥት ፡

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፯ ፡ ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፭

ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡

፳፯ ፤ የአንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ዮሐ ንስ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ልኮ ፡ ለነበረው ፡ መልእክት ፡ መልስ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ ሳት ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ከላከው ፡ መልእክት ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የተገኘ ፤ በአካል ፡ የተለየ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ አምላክ ፡ ቃል በኋላ ፡ ዘመን ፡ እኛን ፡ ስለማዳን ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ያለ ፡ መለወጥ ፡ ንጽሕት ፡ ከምትሆን ፡ ከእመቤታ ችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሰው ፡ እን ደሆነ ፡ እናምናለን ፤ ነባቢት ፡ ለባዊት ፡ ነፍስ ፡ ያለ ችው ፡ ሥጋን ፡ ከእሷ ፡ ነሥቶ ፡ ያለ፡መለያየት ፡ ያለ መለወጥ ፡ በውነት ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡

፳፰ ፤ የእኛን ፡ ሕማም ፡ ታመመ ፤ ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ የእኛን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሠራ ፤ በሚጠራጠር በሚከድ ፡ ሕሊና ፡ የምንናገር ፡ አይደለም ፤ ወንጌ ላዊው ፡ ዮሐንስ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፤ በእኛም ፡ አደረ ብሎ ፡ እንደ ፡ ጻፈ ፡ በውነት ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፡ የተገዥ ፡ ባሕርይን ፡ ገንዘብ ፡ በአደረገ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለት ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሕይወትን ፡ ሊሰጣቸው ፤ የሚድኑበትን ፡ ሕማምን ፡ ሞትን ፡ ሊፈጽምላቸው፡ ሰውን ፡ መስለ ፤ እነዚህም ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት፤ ናቸው ፡

፳፱ ፤ ስለዚህም ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ገዥ ፤ አንድ ፡ ክርስቶስ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንላለን ፡

፴ ፤ በነፍስ ፤ በሥጋ ፤ በሕሊና ፡ ፍጹም ፡ የምትሆን ፤ ከሐዋርያት ፡ የተገኘ ፡ ትምህርትን ፡ በማስተማር ፡ የታወቅህ ፤ ድኅነት ፡ የሚገኝባት ፡ ወንጌልን ፡ የም ታስተምር ፤ በጐ ፡ አባት ፡ ወደ ፡ ተወደደች ፡ ወደ ፍጽምት ፡ ሃይማኖት ፤ ክብርት ፤ ፍጽምት ፡ በምት ሽን ፡ አምልኮ ፡ ምሥጢር ፡ አንድ ፡ ወደምታደርገን ወደ ፡ በጐ ፡ ልጅነት ፤ የምትመራ ፡ ከመናፍቃን ፡ ከሀደት ፡ የተነሣ ፡ ወደማትናወጥ ፤ ጸጥ ፡ ወደ ፡ አለች ፡ ፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ ወደ ፡ ተመላች ፤ ድኅነት ፡ ወደ ፡ ሚገኝባት ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ሰማ ያት ፡ የምታደርስ ፡ መርከብ ፡ ዋጋዋ ፡ ብዙ ፡ የሚሆን ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለባት ፡ ዕንቁ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ሃይማኖት ፡ የምትመራ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ የተወደድክ ፡ ወንድም ፡ ያበረዳንህ ፡ ሃይማኖት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፤ ለዘላለሙ ፡ አሜን ፡

ምዕራፍ ፡ ፪፭ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡

፩ ፤ የእስክንድርያና ፡ የግብጽ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባታ ችን ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፤ ወደ ፡ እሱ ፡ ልኮለት ፡ ለነበ ረው ፡ መልስ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያው ፡ ሊቀ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከላ ከው ፡ መልእክት ፡ በአካል ፡ በገጽ ፡ ሦስት ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲት ፡ ክብር ፤ አንዲት ፡ መን ግሥት ፡ በሚሆን ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፤ ተብሎ ፡ በሚጠራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እናምናለን ፡

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፻፷ ።

፪ ፤ አብሰ ፡ ወላዲ ፡ ውእቱ ፡ ወኢተወላዲ ፡ ወባሕቱ ፡ ወልድ ፡ ተወልደ ፡ ባሕቲቱ ፡ እምአብ ፡ ቅድመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠረጸ ፡ እምአብ ፡ ወዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ በቅድምና ፡ ወምልክና ፡ ወሥልጣን ፡ ወበክሂል ፡ ወበፈጢረ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ኅቡራን ፡ መለኮት ፡ እለ ፡ ርሑቃን ፡ እምኵሉ ፡ ዓቅም ፡ ወኑልቊ ።

፫ ፤ ወኢይቅድም ፡ ፩ዱ ፡ እምካልኡ ፡ ወካልኡ ፡ እምኀልፉ ፡ እላ ፡ ህልዋን ፡ ወጽኑዓን ፡ በ፩ዱ ፡ መለኮት፡ በ፩ዱ ፡ መንግሥት ፡ ወአሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወ፩ዱ ፡ ምግባር ፡ ወአሐቲ ፡ ሥምረት ፡ ወ፩ዱ ፡ ፈቃድ ፡ ወአሐቲ ፡ ስግደት ፡ ወ፩ዱ ፡ አምልኮ ፡ እንተ ፡ ዘይቤ ፡ አካላት ፡ ወይቤ ፡ ገጸት ፡ ተዋሕዶ ፡ ፍጹም ፡ በሥላሴ ፡ ወሥላሴ ፡ ፍጹም ፡ በተዋሕዶ ።

፮ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ፡ ተዋሕዶ በሥላሴ ፡ ፍጹም ፡ ወሥላሴ ፡ በተዋሕዶ ፡ ፍጹም ፡ ጌሰግድ ፡ ሎሙ ፡ አሐተ ፡ ስግደተ ፡ ይቤ ፡ ኤካላት ፡ አለ ፡ ዕሩያን ፡ በክብር ፡ ወበቅድምና ፡ ወበስብሐት ፡ ዘኢይትነገር ፡ ኢፍጡራን ፡ ወኢግዙራን ፡ እላ ፡ እሙንቱ ፡ ፈጣርያነ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወእምኣኢሆሙ ፡ እምኀበ ፡ ኢሀልዎ ፡ ኀበ ፡ ህልዎ ፡ ኅቡራን ፡ ህላዌ ፡ ወሥልጣን ፡ ኢይትፈለጡ ፡ ወኢይትከፈሉ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ እምነ ፡ ግብራት ።

፯ ፤ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ ወንሰብክ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ባሕቲቱ ፡ ኢተወልደ ፡ ወእልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ለሕይወቱ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ወኢይትቈለጥ ፡ ወኢይመውት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ኢልቦ ፡ ጕልቍ ፡ ሲመ ፡ ዕሲዩ ፡ ወአልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለመንግሥቱ ፡ ወኢዐቅም ፡ ለመለኮቱ ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ወፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዘኢያስተርኢ ፡ አብ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ለወልዱ ፡ ዋሕድ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘበቱ ፡ ፈጠረ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ወሆሉ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ መዝ ፡ ፻፬ ፡ (፻፫) ፤ ፲፪—፲፭ ። ሚል ፡ ፫ ፡ ፮ ። ቆላ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።

፰ ፤ ነአምን ፡ ዓዲ ፡ ወንትአመን ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ አካል ፡ እም፫ቱ ፡ አካላት ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ፍጹም፡ ዘአልቦ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጸሜት ፡ ዘኢይትረከብ ፡ በንባብ ፡ ወበልቡና ፡ ወበሕሊና ፡ አላ ፡ ይትሌዐል፡ እምልቡና ፡መዋቲ ፡ ወኢይትከሀለን ፡ ንሕትት ፡ዘከመ እፎ ፡ ውእቱ ፡ ህላዌሁ ፡ ለመለኮት ፡ ወዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ፡ ለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ዋሕድ ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ አዝማን ፡ ወመዋዕል ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ በቅድምና ፡ ወበህልዎ ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፻፷ ።

፪ ፤ አብ ፡ ወላዲ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ተወላዲ ፡ አይደለም፤ ወልድ ፡ ግን ፤ ተቀዳሚ ፤ ተከታይ ፡ ሳይኖረው ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከብቻው ፡ ከአብ ፡ ተወለደ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ ሠረጸ ፡ በቀዳማዊነት ፤ በአገዛዝ ፤ በሥልጣን ፡ በከሀሊነት ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመፍጠር ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ የሚሆኑ ፤ ሦስት ፡ አካላት ፡ ከመወሰን ፤ ከቍጥር ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ የራቁ ፡ ናቸው ።

፫ ፤ አብ ፡ ከወልድ ፡ አይቀድምም ፤ ወልድም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይቀድምም ፤ የሦስቱ ፡ አካላት ፤ የሦስቱ ፡ ገጸት ፡ ገንዘብ ፡ በሚሆን ፡ በአንድ ፡ መለኮት ፡ በአንድ ፡ መንግሥት ፡ በአንድ ፡ ሥልጣን ፡ በአንድ ፡ ሥራ ፤ በአንድ ፡ ውድ ፡ በአንድ ፡ ፈቃድ ፤ በአንዲት ፡ መሰገድ ፤ በአንድ ፡ መመለክ ፡ ጸንተው፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ ፍጹም ፡ አንድነት ፡ በሦስትነት ፡ ፍጹም ፡ ሦስትነትም ፡ በአንድነት ፡ አለ ።

፭ ፤ አንድነትን ፡ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎርዮስ፡ አንድነት ፡ በፍጹም ፡ ሦስትነት ፤ ሦስትነትም ፡ በፍጹም አንድነት ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ አንደ ፡ ተናገረ ፤ አንዲት፡ስግደትን ፡ እንሰግድላቸዋለን ፤ በማይመረመር ፡ ጌትነት ፤ በቀዳማዊነት ፤ በክብር ፡ አንድ ፡ የሚሆኑ ፡ ሦስቱ ፡ አካላት ፡ በፍጹም ፡ ያልተፈጠሩ ፡ ናቸው ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠሩ ፤ ኳለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ ያመጧቸው ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ። በባሕርይ ፡ በሥልጣን ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ ከሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ አይከፈሉም ፤ አይለያዩም ።

፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አባት ፡ የሌለው ፡ እንደሆነ፤ እንዳልተወለደ ፤ ለመገኘቱም ፡ ጥንት ፡ እንዳሌለው እናምናለን ፤ እንታመናለን ፤ አይለወጥም ፡ አይናወጥም ፡ ሞት ፡ ለዘላለሙ ፡ የለበትም ፤ ለዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ የለውም ፤ ለመንግሥቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፤ ለአገዛዙ ፡ ወሰን ፡ የለውም ፤ ሁሉን ፡ የሠራ የሚታየውንና ፤ የማይታየውን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ ነው ፤ ሰማይን ፤ ምድርን ፡ በውስጣቸው ፡ ያለውን ሁሉ ፡ ለፈጠረበት ፡ ለአንድ ፡ ልጁ ፡ ለፈጣሪያችን ለጌታችን ፡ ለመድኃኒታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ አንድ ፡ አባት ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፻፬(፻፫) ፤፲፪—፲፭ ። ሚል ፡ ፫ ፡ ፮ ። ቆላ ፡ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።

፯ ፤ ዳግመኛ ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ለዘመኑ ጥንት ፤ ለአኗኗሩ ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ እንደሆነ ፡ በቃል ፡ የማይነገር ፤ በልብ ፤ በሕሊና ፡ የማይመረመር ፤ በመዋቲ ፡ ሰው ፡ ልቡና ፡ ከመመርመር ፡ የራቀ ፡ ፍጹም ፡ እንደሆነ ፡ እናምናለን ፡ እንታመናለን ፤ የመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ ለመኖር ፡ ከእሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ ከዕለት ፤ ከዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ከአብ ፡ የተወለደ ፤ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ የሌለው ፡ እርሱ ፡ አምላክ ፡ ቃልም ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ልንመረምር ፡ አይቻለንም ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፰ ።

፮ ፤ ወውእቱ ፡ ወልድ ፡ ዘበአማን ፡ ወአምላክ ፡ ዘበአማን ፡ በእንቲአነ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወረደ ፡ እምሰማይ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ እንዘ ፡ ኢይተ ፍሉስ ፡ ወኢይትፈለጥ ፡ እምሕፅነ ፡ አቡሁ ፡ ወእ ንዘ ፡ ኢይከውን ፡ እስትግቡአ ፡ ወዝኁበ ፡ ጎደረ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ድንግል ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ እግዝእትነ ፡ ወተወልደ ፡ እምኔሃ ፡ ልደተ ፡ ዘይት ሌዐል ፡ እምሕሊና ፡ ወይትአዶ ፡ እምልቡና ፡ ወዘ ርሑቅ ፡ እምነ ፡ ደነስ ።

፯፤ እስመ ፡ ይእቲሰ ፡ እንከ ፡ በብሥራተ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ በጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀንሰቶ ፡ ወወ ለደቶ ፡ ወተቀደሰት ፡ ቦቱ ፡ ወነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ አካለ ፡ ሥጋዌ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባ ዊት ፡ ኢያምጽአ ፡ ሥጋ ፡ ምስሌሁ ፡ እምሰማይ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ እምዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ወአብርሃም ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ እንዘ ፡ ኢይፈልስ ፡ እምህላዌሁ ፡ ለከዊነ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ።

፱ ፤ ወኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ እምቀዲሙ ፡ ከመ ፡ ይኅ ድር ፡ ውስቴቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ድያድርስ ፡ ዐላዊ ፡ ወባሕቱ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቦቱ ፡ በኀዲ ፡ ህላዌ ፡ መለኮ ታዊ ፡ ወኮነ ፡ ፩ደ ፡ አካለ ፡ ወፍጹመ ፡ ገጸ ፡ ወፍጹመ ፡ ህላዌ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ በተዋሕዶ ፡ ከመ ፡ ተዋሕዶተ ብርሃን ፡ ምስለ ፡ ዓይን ፡ ወሰሚዕ ፡ ምስለ ፡ እዝን ፡ ወጸዳል ፡ ምስለ ፡ ፀሐይ ፡ ወዋዕይ ፡ ምስለ ፡ እሳት ፡ እስመ ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምዙሉ ፡ ጎደረ ፡ በትሑት ፡ ወዘኢይትገመር ፡ ጎደረ ፡ በዘይትገመር ፡ እስመ ፡ ረቂቅኒ ፡ ዘኢያገምሮ ፡ ምንትኒ ፡ ወለሊሁ ፡ ዘያገ ምር ፡ ዙሉ ፡ ተዋሐደ ፡ በገዚፍ ፡ ወኮነ ፡ ፩ደ ፡ ምስሌሁ ።

፲ ፤ ወኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ተዋሕዶ ፡ በፍናወ ፡ ተውሳክ ፡ ወኢበገጸ ፡ ተሳትፎ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ትድምርት ፡ ከመ ፡ ሑሰት ፡ ዘግቡር ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ርት ዐት ፡ ወቁመት ፡ ወዳእሙ ፡ ተወክፈ ፡ አርአያ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወእንበለ ፡ ተፋልሶ ፡ ወኢትድ ምርት ፡ ወዘእንበለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ወዘእንበለ ፡ ተፈ ልጦ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ ነፍሳዊ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ።

፲፩ ፤ ወለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ አምላክ ፡ እንበለ ፡ ጕልቈ ፡ ዘመን ፡ ወወሰን ፡ ወበደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ተወክፈ ፡ ልደተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢማሰነ ፡ ድንግልናሃ ፡ ለወላ ዲቱ ፡ በልደቱ ፡ እምኔሃ ፡ ወሠሉት ፡ ይእቲ ፡ በድ ንግልናሃ ፡ ዘከመ ፡ ነበረት ፡ እምቅድመ ፡ ትለዶ ፡ ወበከመ ፡ ኢተወለጠ ፡ መለኮቱ ፡ በከዊኖቱ ፡ ሰብአ ፡ ክሣሁ ፡ ለደንግልሂ ፡ ኢተወለጠ ፡ ማኅ ተመ ፡ ድንግልናሃ ፡ እምድኅረ ፡ ፀአተ ፡ ሕፃን ፡ እምኔሃ ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፰ ።

፮ ፤ የባሕርይ ፡ ልጅ ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ኤርሱ ፡ ስለ እኛ ፤ እኛን ፡ ስለማዳን ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ሳይለወጥ ፤ ከአባቱ ፡ አንድነት ፡ ሳይለይ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ሕጸጽ ፤ ውሳኔ ፡ ሳይኖርበት ፡ በእመቤታችን ፡ በቅ ድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕፀን ፡ አደረ ፤ በሕ ሊና ፡ ከመታሰብ ፡ በልቡና ፡ ከመመርመር ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ በዘር ፡ ከመወለድ ፡ የራቀ ፡ ልደትን ፡ ከእ ስዋ ፡ ተወለደ ።

፯ ፤ እንግዲህ ፤ እርሷ ፡ በመልአኩ ፡ ብሥራት ፤ በመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቸርነት ፡ ፀንሳ ፡ ወለደችው ፡ እርሱ ንም ፡ በመውለድዋ ፡ ከበረች ፤ ነባቢት ፤ ለባዊት ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ሥጋዊ ፡ አካልን ፡ ከእሷ ፡ ነሣ ፤ ሥጋን ፡ ከሰማይ ፡ አላመጣም ፤ ከዳዊትና ፡ ከአብ ርሃም ፡ ባሕርይ ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ተዋሐደ ፡ እንጂ ፤ ስለዚህም ፤ ቃል ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ ከባሕርዩ ፡ ሳይለወጥ ፡ ሰው ፡ ሆነ ።

፱ ፤ ከሐዲ ፡ ድያድርስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ ቃል ፡ ይዋሐ ደው ፡ ዘንድ ፡ በቅድምና ፡ ሥጋ ፡ አልነበረም ፤ አንድ ፡ የአምላክ ፡ ባሕርይ ፡ አድርጎ ፡ ተዋሐደው ፡ እንጂ ፤ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ በመዋሐዱም ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ ከዓይን ፡ መስ ማት ፡ ከጆሮ ፡ እንዲዋሐድ ፡ ሥጋን ፡ በመዋሐድ ፤ ጸዳል ፡ ከፀሐይ ፡ ዋዕይ ፡ ከእሳት ፡ እንዳይለይ ፤ ባለ ፡ መለየት ፡ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ ባሕ ርይ ፡ ሆነ ፤ ከሁሉ ፡ ልዑል ፡ የሚሆን ፡ መለኮት ፡ ትሑት ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶአልና ፡ የማይወሰን ፡ መለኮት ፡ የሚወሰን ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶአልና ፡ ምንም ምን ፡ የሚወስነው ፡ የሌለ ፤ ሁሉን ፡ የሚወስን ፡ ረቂቅ ፡ እርሱ ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ከእር ሱም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነ ።

፲ ፤ ይህ ፡ ተዋሕዶ ፡ በኅድረት ፡ አንድነት ፡ በመቀላቀል ፡ ሥራ ፡ የሆነ ፡ አይደለም ፡ ይህቺውም ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ መቀላቀል ፡ ያለች ፡ መጽናት ፡ መቅ ናት ፡ የሌላት ፡ መቀላቀል ፡ ናት ፡ መለወጥ ፡ ባሕ ርዩን ፡ መልቀቅ ፡ መቀላቀል ፤ ሳይኖርበት ፤ የአባት ፡ ዘር ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆነው ፤ ከእኛ ፡ ከነሣው ፤ ነፍስ ፡ ካለችው ፡ ሥጋ ፡ መለየት ፡ ሳይኖርበት ፤ የእኛን ፡ ባሕርይ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፡ እንጂ ።

፲፩ ፤ ዘመን ፡ ሳይቈጠርለት ፤ ዘመን ፡ ሳይወስነው ፡ ከአብ ፡ የተወለደ ፤ በኋላ ፡ ዘመንም ፡ ለሰው ፡ የሚገባ ፡ ልደ ትን ፡ የተወለደ ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ አምላክ ፡ ስለሆነ ፤ ከእርስዋ ፡ በመወለዱ ፡ የእናቱ ፡ ድንግልና ፡ አልተለወጠም ፤ ሳትወልደው ፡ እንደ ፡ ነበረችው ፡ በድንግልና ፡ ጸንታ ፡ ያለች ፡ ናት ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ መለኮቱ ፡ እንዳልተለወጠ ፤ እንደዚሁም ፡ እርሱ ፡ ሕፃን ፡ ክርስቶስ ፡ ከእሷ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፤ ማኅ ተመ ፡ ድንግልናዋ ፡ አልተለወጠም ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፭ ።

፲፪ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወላዲተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይእቲ ፡ ዘበአማን ፡ ወዘተወልደ ፡ እምኔሃ ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡ ዘተዋሐደ ፤ ብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ፩ዱ ፡ መሢሕ ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ እምኔሃ ፡ ወኢ ወሰከ ፡ በጕልቈ ፡ ሥላሴ ፡ አካለ ፡ ራብዐየ ፡ በእንተ ፡ ዘለብሰ ፡ ሥጋነ ፡ ውእቱሰ ፡ ፅሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወይትዔረየነ ፡ ለነ ፡ በትስብእት ፡ ወኢፈለሰ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ኀበ ፡ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ ገብረ ፡ መንክራት ፡ በመለኮቱ ፡ ወሐመ ሕማመ ፡ ዚአነ ፡ በትስብእቱ ።

፲፫ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ የሐንስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወንጌላዊ ፡ እስመ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ተሳተፉ ፡ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ወከመዝ ፡ ተመሰሎሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ያብዋል ፡ በሞቱ ፡ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ ወከመ ፡ ያግዕዘነ ፡ እምተቀንዮ ፡ ለሰይጣን ፡ ወየሀበነ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።

፲፬ ፤ ዕበሰ ፡ ኢተሳተፈነ ፡ በትስብእቱ ፡ ወበተሠግዎቱ ፡ ሐማሚ ፡ እምኢክህለ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሕማም ፡ ረኪቦቶ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወባሕቲ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ዘነ ፡ ሥአ ፡ እምኔነ ፡ እስመ ፡ መለኮትሰ ፡ ልዑል ፡ ወነ ኪር ፡ እምዝንቱ ፡ ወኢይቀርቦ ፡ ሕማም ፡ ወሞት ፡ ለግሙራ ፡ ወለሊሁ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በኃይል ፡ መለኮቱ ፡ ወውእቱ ፡ ያሐምሞ ፡ ለሕማም ፡ ወያማስን ፡ ሥልጣነ ፡ ኖት ፡ ወባሕቲ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ተወክፈ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ ወተዋሐደ ፡ ምስሌነ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ መለኮቱ ፡ እምትስብእቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ ፡ በእንቲአነ ፡ በሥጋ ፡ ወውእቱ ፡ ሕያው ፡ በመንፈስ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፭ ፤ ወከመዝ ፡ ዓዲ ፡ መሀረነ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዐቢይ ፡ ዘአለ ፡ እስክንድርያ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዕበ ፡ ሐመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሥጋ ፡ ኢተፈልጠ ፡ እምኔሁ ፡ መለኮት ፡ ወቅዱስሰ ፡ አግናዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ንጹሐን ፡ ይብል ፡ በመልእክቱ ፡ እንተ ፡ ጸሐፋ ፡ ወፈነዋ ፡ ኅበ ፡ ሀገረ ፡ ሮምያ ፡ ኅድጉኒ ፡ ይእዜ ፡ እትመሰሎ ፡ በሕማም ፡ ወምንዳቤ ፡ ለአምላኪየ ።

፲፮ ፤ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ቴዎሎስ ፡ በድርሳኑ ፡ በእንተ ፡ ሕማሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ንሕነሰ ፡ ፈቀድነ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይሙት ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ንሕየው ፡ በሞቱ ዚአሁ ፡ ወበሕይወቱ ፡ ወበከመ ፡ ተሰደድነ ፡ ወሞትነ ፡ ምስሌሁ ፡ ተሰባሕነ ፡ ምስሌሁ ፡ ወተንሣእነ ፡ በትንሣኤሁ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ እንተ ፡ ፈነዋ ፡ ኅበ ፡ አቅላንድዮስ ፡ እመቦ ፡ ዘኢየአምን ፡ ወኢይሰግድ ፡ ለዘተሰቅለ ፡ በእንቲአነ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፭ ።

፲፪ ፤ ስለዚህም ፤ እርሷ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ ናት ፤ ከእሷም፡ የተወለደው ፡ ፍጹም ፡ ነፍስን ፤ ሥጋን ፡ የተዋሐደ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ከእርሷ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር፡ቃል ፡ አንድ ፡ መሢሕ ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ ነው ፤ ሥጋችንን ፡ ስለ ፤ ተዋሐደ ፡ በሦስትነት፡ ላይ ፡ ዐራተኛ፡ አካልን ፡ አልጨመረም ፤ እሱ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ሰው ፡ በመሆኑም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ የሥጋ ፡ ባሕርይ ፤ የመለኮት ፡ ባሕርይን ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ አልተለወጠም ፤ አምላክ ፡ ነውና ፡ ተአምራትን፡ አደረገ ፤ ሰው ፡ በመሆኑም ፡ የእኛን ፡ ሕማም ፡ ታመመ ።

፲፫ ፤ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፡ በእኛም ፡ አደረ ፤ ብሎ ፡ እንደ፡ ተናገረ ፤ ጻግመኛም ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፤ ልጆች ፡ ሥጋ ፡ ደም ፡ በመሆን ፡ አንድ ፡ እንደሆኑ ፡ እንዲሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መሰላቸው ፤ በሞቱ ፡ የሞትን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፤ ለሰይጣን ፡ ከመገዛትም ፡ ነፃ ፡ ያወጣን ፡ ዘንድ ፤ የዘለዓለም ፡ ድኅነትንም ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ አለ ። ዮሐ፡ ፩ ፡ ፲፬ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።

፲፬ ፤ ሕማም ፡ የሚስማማው ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ባይመስለን ፡ ኖሮስ ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ሕማም ፡ ሊያገኘው ፡ ባልቻለም ፡ ነበር ፤ ከእኛ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፤ ታመመ ፡ እንጂ ፡ መለኮትስ ፡ ከዚህ ፡ ፈጽሞ ፡ የራቀ ፤ ነው ፤ ሕማምና ፡ ሞትም ፡ ፈጽሞ ፡ አያገኘውም ፡ በጌትነቱ ፡ ሥልጣን ፡ አሉ ፡ ያጠፋቸዋል ፤ እሱ ፡ ሕማምን ፡ ይሽራል ፤ የሞትንም ፡ ሥልጣን ፡ ያጠፋል ነገር ፡ ግን ፤ ከእኛ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ መለኮቱ ፡ ከትስብእት ፡ ሳይለይ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነ ፤ ስለዚህም ፤ ሐዋርያው ፡ ጴጥሮስ ፤ በሥጋ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ እንደሆነ ፡ ተናገረ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፭ ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፤ ደገኛው ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ አትናቴዎስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሥጋ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፤ መለኮት ፡ ከሥጋ ፡ አልተለየም ፤ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አስተማረን ፤ የንጹሐን ፡ ሐዋርያት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ አግናጥዮስም ፡ ጽፎ ፡ ወደ ፡ ሮም በላካት፡መልእክቱ፡ተውኝ ፤ዛሬ፡ፈጣሪዬ፡ክርስቶስን፡ በሕማምና ፡ በጭንቅ ፡ መከራ ፡ ልምሰለው ፡ ብሏል ።

፲፮ ፤ ጻግመኛም ፤ አንድነትን ፤ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎርዮስም ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፤ የሕማሙን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ ድርሳኑ ፤ እኛስ ፡ በእርሱ ፡ ሞት ፤ በትንሣኤውም ፡ እንድን፡ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በሥጋ ፡ ሊሞት ፡ ወደደን ፡ እርሱን ፡ አብነት ፡ አድርገን ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተቀበልን ፡ እንደ ፡ ሞትን ፤ በእርሱ ፡ ከብር ፡ ከበርን ፤ በትንሣኤውም ፡ ተነሣን ፡ አለ ፤ ጻግመኛም ፤ ወደ ፡ አቅላንድዮስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ለተሰቀለው ፡ የማይሰግድ ፡ ቢኖር ፡ ወጉዝ ፡ ይሁን ፡ ብሏል ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፰ ።

፲፯ ፤ ወዮሐንስኒ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢያስተርኢ ፡ ወዘኢያአምር ፡ መኑሂ ፡ ብርሃኖ ፡ ወዘኢይትነገር ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ፡ ተሰቅለ ፡ ወተኮነነ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይቤዝወነ ፡ ወአንዘ ፡ ባዕል ፡ ውእቱ ፡ አንደየ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይሚጠነ ፡ ጎበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ርስትነ ፡ ወቅዱስሂ ፡ ማሪ ፡ ኤፍሬም ፡ ይብል ፡ በመጽሐፉ ፡ ዘይሰመይ ፡ መርጋሪዳስ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ዕንቁ ፡ ሐሰ ፡ ለከ ፡ ትበል ፡ አው ፡ እበል ፡ አነ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐመ ፡ በሀላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወሐሰ ፡ ሊተ ፡ እበል ፡ ከመ ፡ አድኅነ ፡ ብእሲ ፡ ዕሩቅ ፡ ፍጡራነ ።

፲፰ ፤ ወቅዱስሂ ፡ ኤራቅሊስ ፡ ዘፈለሰ ፡ እምኪስኪስ ፡ ጎበ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ይብል ፡ በድርሳኑ ፡ በእንተ ፡ ልደቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ህልው ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ አቡሁ ፡ በአርያም ፡ ህልው ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ድንግል ፡ በተዋሕዶ ፡ ወለሊሁ ፡ ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ እንዘ ፡ ህሎ ፡ ይሴባሕ ፡ እምነ ፡ መላእክት ፡ ውስተ ፡ ሉዓሌ ፡ ሰማያት ፡ ወበምድርኒ ፡ ውእቱ ፡ ሕቁፍ ፡ በሕፅነ ፡ ድንግል ፡ ዘሱራፌል ፡ ኢይክሉ ፡ ነጽሮተ ፡ ገጹ ፤ ቅድመ ፡ ጲላጦስ ፡ መስፍን ፡ ቆመ ፡ ለተሐቶ ፡ ከመ ፡ ዘእቡስ ፡ ገብር ፡ እኩይ ፡ አጽንዐ ፡ እዴሁ ፡ ወጸፍአ ፡ ገጸ ፡ ፈጣሪሁ ፡ ዘይርዕዱ ፡ ዙሉ ፡ ፍጥረት ፡ እምኔሁ ፡ ወዘይነብር ፡ መልዕልተ ፡ አርያም ፡ ተሰቅለ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ከመ ፡ ያዐቅ ፡ ወያጠይቅ ፡ በዝንቱ ፡ ወይክሥቶ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ፭ዱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ውእቱ ።

፲፱ ፤ ጳውሎስኒ ፡ ሐዋርያ ፡ ይቤ ፡ ሶበሰ ፡ አእመርዎ ፡ ከመ ፤ ውእቱ ፡ እግዚአ ፡ ስብሐት ፡ እምኢሰቀልዎ ፡ ወእምነ ፡ እሉ ፡ ከሚቶታት ፡ ወሰምዓት ፡ ጽዱቃት እንተ ፡ ዘአበው ፡ ንጹሓን ፡ ነአምን ፡ ወንት አመን ፡ ክመ ፡ ክርስቶስ ፡ ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ በመለኮቱ ፡ ሉአላዊት ፡ ወበትስብእቱ ፡ ትሕት ፡ ምድራዊት ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፰ ፡ መዝ ፡ ፸፬ ፡ (፸፫)፰ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ። ያዕ ፡ ፪ ፡ ፩ ።

፳ ፤ ወነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ፤ ወዘስንዕው ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወቦቱ ፡ አካል ፡ ፍጹም ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘደሰያት ፡ እስመ ፡ አብ ፡ ህልው ፡ በአካሉ ፡ ወበገጹ ፡ ወወልድኒ ፡ ህልው ፡ ከማሁ ፡ በአካሉ ፡ ወበገጹ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ህልው ፡ በአካሉ ፡ ወበገጹ ፡ ወዓዲ ፡ ነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወአኮ ፡ ነኪር ፡ ውእቱ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮተ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ሐሰ ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፰ ።

፲፯ ፤ አፈወርቅ ፡ የተባለ ፡ ዮሐንስም ፤ የማይታይ ፡ ባሕርዩንም ፡ ማንም ፡ ማን ፡ የማያውቀው ፤ እንደምንም እንደሆነ ፡ የማይነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ተሰቀለ ፤ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ ተፈረደበት ፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ሲሆንም ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ቦታችን ፡ (ወደገነት) ፡ ይመልሰን ፡ ዘንድ ፡ ራሱን ፡ ድኅ ፡ አደረገ ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬምም ፡ ትርጓሜው ፡ ዕንቁ ፡ ማለት ፡ በሚሆን ፡ መርጋሪዳስ ፡ በሚባል ፡ መጽሐፉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ታመመ ፡ ብለህ ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ አይገባህም ፡ ለእኔም ፡ ልናገር ፡ አይገባኝም ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲም ፡ ፍጡራንን ፡ አዳነ ፡ ብዬ ፡ ልናገር ፡ አይገባኝም ፤ ይላል ።

፲፰ ፤ ከኪስኪስ ፡ ወደ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ያለፈ ፡ ቅዱስ ፡ ኤራቅሊስም ፤ የክርስቶስን ፡ የልደቱን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ ድርሳኑ ፤ በልዕልና ፡ በአባቱ ፡ ዕሪና ፡ ሳለ ፤ በተዋሕዶ ፡ በድንግል ፡ ማሕፀን ፡ ተወስኖ ፡ አለ ፤ እርሱ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ በልዑል ፡ ሰማይ ፡ ከመላእክት ፡ ሲመሰገን ፡ ሳለ ፡ በምድርም ፡ በድንግል ፡ ክንድ ፡ ተወስኖ ፡ ተይዟል ፤ ሱራፌል ፡ ፊቱን ፡ ሊያዩት ፡ የማይችሉ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ በደለኛ ፡ ለመመርመር ፡ በመስፍኑ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ ቆመ ፡ ክፉ ፡ ባርያ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ከማርማው ፡ የተነሣ ፡ የሚንቀጠቀጡለትን ፡ የፈጣሪውን ፡ ፊት ፡ በጥፊ ፡ መታ ፤ በዚህም ፤ እርሱ ፡ ተቀዳሚ ፤ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ወልድ ፡ እንደሆነ ፡ ይገልጥልን ፤ ያስረዳን ፤ ያስታውቀን ፡ ዘንድ ፡ በልዕልና ፡ የሚኖር ፡ እርሱ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ፡ አለ ።

፲፱ ፤ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ እንደሆነ ፡ ቢያውቁት ፡ ኖሮስ ፡ ባልሰቀሉትም ፡ ነበር ፤ ብሏል ፤ ንጹሓን ፡ አበው ፡ ከተናገሩዋቸው ፡ ከተረዱ ፡ ምስክሮችና ፡ ከእነዚህ ፡ አገላለጦች ፡ የተነሣ ፡ ክርስቶስ ፡ በልዑል ፡ ባሕርዩና ፡ በምድር ፡ በተገኙ ፡ በትሑት ፡ ባሕርዩ ፡ መለያየት ፡ የሌለበት ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ እናምናለን ፡ እንታመናለን ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ለርሱ ፡ ይሁን ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፰ ፡ መዝ ፡ ፸፬ ፡ (፸፫) ፡ ፰ ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ። ያዕ ፡ ፪—፩ ።

፳ ፤ ከአብ ፡ በሠረጸ ፤ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ በሚሆን ፤ እንደ ፡ አብ ፡ እንደ ፡ ወልድ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ ባለው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እናምናለን ፡ የደቤቶቹ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፤ አብ በአካሉ ፤ በገጹ ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ወልድም ፡ እንደ ፡ አብ ፡ በአካሉ ፤ በገጹ ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በአካሉ ፡ በገጹ ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ነው እንዳለ ፤ ዳግመኛም ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ አኩል ፡ ትከክል ፡ እንደሆነ ፤ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ ልዩ ፡ እንዳይደለ ፡ እናምናለን ፤ ልዩ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይገባም ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፫ ።

ሸ፩ ፤ ወባሕቱ ፡ ነአምሮ ፡ ለአብ ፡ ከመ ፡ ኢተወላዲ ፡ ውእቱ ፡ ወወልድሂ ፡ ተወላዲ ፡ ውእቱ ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስሂ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ፡ ወዕሩይ ፡ ምስሌሆሙ፡ በህላዌ ፡ ወበስብሐት ፡ ወኅዲ ፡ ነአምን ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ስምዐ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ጊዜ ፡ ከሠተ ፡ ግብሮ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እፌኑ፡ለክሙ ፡ ጰራቅሊጦስሃ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ እምአብ ፡ ዘይወፅእ ፡ ወውእቱ ፡ ይነግረክሙ ፡ ኵሎ ፡ ወበዝንቱ ፡ ንባብ ፡ አጠየቀ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ እመለኮተ ፡ አብ ፡ ወወልድ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ።፲፮ ፡ ፯—፲፬ ።

ሸ፪ ፤ ሥላሴ ፡ ህልዋን ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ በፆዱ ፡ መለኮት ፡ ወበአሐቲ ፡ መንግሥት ፡ ወበፆዱ ፡ ስባሔ ፡ ተዋሕዶ ፡ በሥላሴ ፡ ወሥላሴ ፡ በተዋሕዶ ፡ ወነአምን ፡ በዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ በሕሊና ፡ ጽድቅ ፡ ወበልብ ፡ ንጹሕ ፡ ወጽሩይ ።

ሸ፫ ፤ ወኅዲ ፡ ንትአመን ፡ ቦሙ ፡ በቃል ፡ ወበምግባር ፡ እምነተ ፡ ጽድቅተ ፡ ወናስተበቍዕ ፡ ኅቤሆሙ ፡ ከመ ፡ ያፈድፍዱ ፡ አእምሮቶሙ ፡ ዲቤነ ፡ ወከመ ፡ ይኩኑነ ፡ መራሕያነ ፡ ፍኖት ፡ ርትዕት ፡ ከመ ፡ ንር ከብ ፡ ፍኖተ ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ለገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ዘንትዌደስ ፡ ባቲ ፡ በደኃሪትነ ፡ ወከመ ፡ ይሕንጹ ፡ ደኃሪተነ ፡ በሠናይ ፡ ሕንጻ ፡ ላዕለ ፡ መሠረት ፡ ጽኑዕ ፡ ዘኢያንቀለቅል ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሕንጻ ፡ መምህራን ፡ ትሩፋን ፡ ወባቲ ፡ ናጽንዕ ፡ ሃይማኖተነ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሚተ ፡ ሕይወትነ ፤ ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ሸ፬ ፤ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአቡነ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ኅበ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእንጾኪያ ፡ በ፱ቱ ፡ ፪ ወ፫ቱ ፡ እምዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ንሕነሰ ፡ ይእዜ ፡ ነአምን ፡ ፭ዱ ፡ አፍ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ወኢተሌልዮ ፡ በኀይሉ ፡ ወበረድኤቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፪፫ ።

ሸ፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የተወለደ ፡ እንዳይደለ ፡ አብን ፡ እናውቀዋለን ፤ ወልድ ፡ ግን ፡ ተወላዲ ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ የሠረጸ ፡ ነው ፤ በባሕርይ ፤ በጌትነትም ፡ ከአብ ፤ ከወልድ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ዳግመኛም ፤ የእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ እሱ እንደሆነ፡ እናምናለን ፤ አምላክ፡ቃል ፡ ለደቂ፡ መዛሙርቱ ፡ አምላክነቱን ፡ በገለጠላቸው ፡ ጊዜ ፤ ከአብ ፡ የሠረጸ ፡ ባሕርያዊ ፤ አካላዊ ፡ እስትንፋስ ፡ ጸራቅሊጦስን ፡ እሰድላችኋለሁ ፤ እሱም ፡ ሁሉን ፡ ይነግራችኋል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ መሰከረለት ፤ በዚህም ፡አነ ጋገር ፡ እርሱ ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ማይለይ ፡ አስረዳ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ፡ ፲፮ ፡ ፯—፲፬ ።

ሸ፮ ፤ ሥላሴ ፡ ሳይለያዩ ፡ በአንድ ፡ መለኮት ፤ በአንዲት ፡ መንግሥት ፤ በአንድ ፡ ክብር ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ አንድነት ፡ በሦስትነት ፤ ሦስትነት ፡ በአንድነት ፡ አለ ፤ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ በተረዳ ፡ ዕውቀት ፤ ጥሩ ፤ ንጹሕ ፡ በሆነ ፡ ልቡና ፡ እናምናለን ።

ሸ፯ ፤ ዳግመኛም ፤ በቃል ፤ በሥራ ፤ የተረዳች ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖትን ፡ እናምንባቸዋለን ፡ ዕውቀታቸውንም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ያሳድሩብን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡ እንማልዳለን ፤ በዘመናችን ፡ ፍጻሜ ፡ የምንመሰገንባትን ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ የምታበቃ ፡መንገድን ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ይመሩን ዘንድ ፤ ፍጻሜአችን፡በማይናወጥ ፤ በጸና ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ በበጎ ፡ ምግባር ፡ ያጸኑልን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እነሱ፡እንማልዳለን ፤ይህቺውም፡ ፍጹማን ፡ መምራን ፡ ያስተማሩዋት ፡ ትምህርት ፡ ናት ፤እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ በርሷ ፡ እናጽና ፤ ለጌታችን ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ አሜን ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ሸ፰ ፤ ሰማዕታት፡ በተነሡ ፡ በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፤ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባታችን ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ወደ ፡ እንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ጽፎ ፡ ከላከው ፡ መልእክት ፤ እኛስ ፤ ዛሬ ፡ በጌታችን ፡ በፈጣሪያችን ፤ በመድኃኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጋዥነት ፡ ከሀሊነት ፤ ያለ ፡ መለያየት ፡ ያለ ፡ መከፋፈል ፤ አንድ ፡ ልብ ፤ አንድ ፡ አፍ ፡ ሆነን ፡ እናምናለን ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፮፮ ።

ፍ፮ ፤ ወነአምን ፡ ዓዲ ፡ በጥበብ ፡ ወበሕሊና ፡ በ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ አብ ፡ አጋዜ ፡ ዙሉ ፡ ወፈጣሬ ፡ ዙሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዘኢያስተርኢ ፡ ወበ ወልዱ ፡ ዋሕድ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእነ ፡ ወሀቤ ፡ ሕይወት ፡ ሥላሴ ፡ እለ ፡ ዕሩያን ፡ በአካላት ፡ በ፩ዱ ፡ ክብር ፡ ወበ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ ወበ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ወኢተሌልዮ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ንጹሓን ፡ እንዘ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ በገቢር ፡ ውኅይል ፡ ፩ዱ ፡ መንግሥት ፡ ወአሐቲ ፡ ምክር ፡ ወአሐቲ ፡ ስባሔ፡ ወ፩ዱ ፡ ምልክና ፡ ወ፩ዱ ፡ ህሉና ፡ ወ፩ዱ ፡ ሥል ጣን ፡ ወ፩ዱ ፡ እግዚእነ ፡ ዘቮቱ ፡ አካላት ፡ ወቮቱ ፡ ገጸት ፡ ዘውኦቶሙ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ፍ፯ ፤ እስመ ፡ ለተዋሕዶተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመለ ኮት ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚ እነ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሠቶ ፡ ለነ ፡ በወንጌሉ ፡ ቅዱስ ፡ ጎበ ፡ ይብል ፡ አነ ፡ እስእሎ ፡ ለአቡየ ፡ ከመ ፡ ይፈኑ ለክሙ ፡ ጸራቅሊጦስሃ ፡ ዘውእቱ ፡ ካልኣ ፡ አካል ፡ ዘከማየ ፡ ይትጎፈሩ ፡ እንከሰ ፡ ዝየ ፡ ይእዜ ፡ አብ ስልዲስ ፡ ወመቅዶንዮስ ፡ እለ ፡ ኢይሁቡ ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ፡ ለመካፈስ፡ ቅዱስ፡ እስመ፡ ብሂ ልሰ ፡ ካልእ ፡ ዘከማየ ፡ ይከሥት ፡ ለነ ፡ ፍልጠተ ፡ አካላት ፡ ወብሂለ ፡ ቃልሂ ፡ እፌኑ ፡ ለክሙ ፡ ጸራ ቅሊጦስሃ ፡ እምዚአየ ፡ ይነሥእ ፡ ወይነግረክሙ ፡ ይሜህረነ ፡ በዝንቱ ፡ ሱታፌ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለ ኮት ፡ ወዝንቱሰ ፡ ቃል ፡ ይዘልፎሙ ፡ ለሰባልዮ ሳውያን ፡ ወለአርዮሳውያን ፡ ዐላውያን ፡ ተቃራ ንያነ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ እለ ፡ ዕሩያን ፡ በመለኮት ።

ፍ፰፤ ንሕነሰ ፡ ነአምን ፡ ቦሙ ፡ ወንሴብሖሙ ፡ አሐተ፡ ስባሔ ፡ ወናመልኮሙ ፡ እንበለ ፡ ሌልዮ ፡ በ፩ዱ፡ መለኮት ፡ ወበአሐቲ ፡ ስግደት ፡ ወእለሰ ፡ ይፈል ጥዎሙ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይሴብሑ ፡ ካልአ ፡ አምላክ ፡ እምዝንቱ ፡ ወይትአመኑ ፡ ነኪራን ፡ ወውጉዛን ፡ እሙንቱ ፡ ወምኑናን ፡ በጎቤነ ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፮፮ ።

ፍ፮ እንዲሁም ፤ በጥበብ ፡ በዕውቀት ፡ ጸንተን ፡ የሚታ የውንና ፡ የማይታየውን ፤ ፍጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ በፈ ጠረ ፤ ሁሉን ፡ በሚገዛ፡ በአንድ ፡ አምላክ ፡ በአብ ፡ ተቀዳሚ ፤ ተከታይ፡ በሌለው፡ በልጁ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፤ ሕይወትን ፡ በሚያድል፤ በጌታችን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እናምናለን ፡ ሥላሴ፡ በአንድ፡ ክብር ፤ በአንድ፡ መለኮት ፤ በአንድ ፡ ባሕርይ ፤ ፈጽሞ ፡ ባለመለየት ፡ አንድ ፡ የሚሆኑ ፡ ንጹሓን ፡ ባሕርይ ፡ ሦስት ፡ አካላት ፡ ናቸው ፤ ፍጥ ረትን ፡ በመፍጠር ፤ በከሃሊነት ፡ አንድ ፡ አምላክ ሲሆን ፤ የሦስቱ፡አካላት ፤ የሦስቱ ፡ ገጸት ፡ ጌትነት፡ አንድ ፡ ነው ፤ ሥልጣናቸው ፡ አንድ ፡ ነው፤ አኗኗ ራቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ አገዛዛቸው ፡ አንድ፡ ነው ፡ ክብራቸው ፡ አንዲት ፡ ናት፡ ምክራቸው ፡ አንዲት፡ ናት ፤ መንግሥታቸውም፡አንድ፡ ነው ፤ እነዚህም ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ።

ፍ፯ ፤መንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መሆኑንም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፤ በአካል ፡ ልዩ ፡ የሆነ ጸራቅሊጦስን ፡ ይሰድላችሁ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ አባቴን፡ እለምነዋለሁ ፡ ብሎ ፡ በተናገረበት ፡ በወንጌል ፡ ለእኛ ፡ ገልጦልክል ፤ እንኪያስ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ የማያቀርቡ ፡ እነዚህ ፡ መቅዶ ንዮስና ፡ አብስልዲስ ፡ አሁን ፡ ይፈሩ ፤ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ማለት ፡ የአካላትን ፡ ሦስትነት፡ ያስረዳል፤ አካላዊ ፡ ቃልም ፡ ጸራቅሊጦስን ፡ እሰድላችኋለሁ ፤ ቃልነትንም ፡ ከእኔ ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ይነግራች ኋላ ፡ ማለቱ ፤ በዚህ ፤ በመለኮት ፡ አንድነት ፡ ያለ ውን ፡ አንድነት ፡ ያስተምረናል ፤ ይህም ፡ ቃል ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ የሚሆኑ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስን ፡ የሚ ቃወሙ ፡ የአርዮስና ፡ የሰባልዮስ ፡ ወገኖች ፡ የሚ ሆኑ ፡ መናፍቃንን ፡ ይዘልፋቸዋል ።

ፍ፯ ፤ እኛ ፡ ግን ፤ እናምንባቸዋለን ፡ እንዲት ፡ ምስጋናን ፡ እናመሰግነዋለን ፡ በአንድ ፡ መለኮት ፡ ባለመለ ያየት ፡ እናመልካቸዋለን ፤ አንዲት ፡ ስግደትን ፡ እን ሰግድላቸዋለን ፡ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ በማበላለጥ ፡ የሚያመልኩ ፤ የሚታመኑ ፡ግን ፡ በማኅበራችን ፡ ተወግዘው ፡ የተለዩ ፤ የተጠሉ ፡ ናቸው ።

ዘዘካርያስ ፡ ም ፡ ፻፷ ።

፳፷ ፤ ወይእዜኒ ፡ ይደልወነኬ ፡ ከመ ፡ ንትናገር ፡ በእንተ ፡ ትሥጉቱ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዘውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ዘኢፍጡር ፡ ወኢግቡር ፡ ወኢፍሉጥ ፡ እመለኮተ ፡ አቡሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አምላክ ፡ ንሕነሰ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ነአምን ፡ እንበለ ፡ ጽንት ፡ ወኢተወላውሎ ፡ በወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ጥንት ፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘዕሩይ ፡ በመለኮቱ ፡ ዘኢይትገመር ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ በእንቲኣነ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ተወልደ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ በከመ ፡ መሀረነ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዘመን ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ወኮነ ፡ ምስሌነ ። ገላ ፡ ፬ ፡ ፬ ።

